ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሐ-ግብር

# የግራኝነት እምነታዊና ማህበራዊ ፍልስፍና ትንተና በካፋ ብሔረሰብ ተተኳሪነት

በ

ሰለሞን ወንድሙ ገብሬ

2016ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# የግራኝነት እምነታዊና ማህበራዊ ፍልስፍና ትንተና በካፋ ብሔረሰብ ተተኳሪነት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ  (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሐ-ግብር

በኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት ጥናታዊ ፅሑፍ

<u>አማካሪዎች</u>

ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)

ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

ግንቦት / 2016ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

ምስጋና ....................................................................................................................i

የካፊኛ ቃላት አቻ የአማርኛ ትርጉም ..........................................................................ii

አጠቃሎ .................................................................................................................... iii

ምዕራፍ አንድ..............................................................................................................1

መግቢያ.........................................................................................................................1

1.1. የጥናቱ ዳራ.............................................................................................................2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት..........................................................................................4

1.3. የጥናቱ ዓላማ..........................................................................................................5

1.4. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች .............................................................................................5

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ .....................................................................................................5

1.6. የጥናቱ ወሰን..........................................................................................................6

1.7. የመስክ ተሞክሮ ......................................................................................................7

ምዕራፍ ሁለት ...............................................................................................................8

ክለሳ ድርሳናት................................................................................................................8

2.1. ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝት ...................................................................................................8

2.1.1. የፎክሎር ምንነት.....................................................................................................8

2.1.2. የሀገረሰባዊ ልማድ ምንነት .........................................................................................9

2.1.2.1. ትዕምርት (symbol).............................................................................................10

2.1.2.2 ሚልኪ ................................................................................................................11

2.1.2. የግራኝና ግራኝነት ብያኔ .........................................................................................11

2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት..................................................................................................14

2.2.1. ፍካሬ ልቡናዊ ንድፈ ሀሳብ (Psychoanalytical theory) .................................15

2.2.2. የትዕምርታዊነት ንድፈ ሀሳብ (symbolic Theory)............................................15

2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.........................................................................................16

ምዕራፍ ሶስት ....................................................................................................19

የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ........................................................................................19

3.1 የጥናቱ ስልት ............................................................................................19

3.2. የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ ...........................................................19

3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች .....................................................................21

3.3.1 ቃለመጠይቅ.........................................................................................21

3.3.2 ሰነድ ፍተሻ .........................................................................................22

3.4. የመረጃ መቅረጫ መሳሪያዎች.....................................................................23

3.5. የመረጃ አደረጃጀት ...................................................................................24

3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ................................................................................24

3.7. የጥናቱ ስነምግባራዊ ጉዳዮች.......................................................................25

ምዕራፍ አራት ....................................................................................................26

የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ .....................................................................................26

4.1. መልካዓ ምድራዊ ዳራ ...............................................................................26

4.2.የካፋ ብሔረሰብ ጥንተ አመጣጥ ታሪክ ...........................................................27

4.3. ጥንታዊ ነገስታትና የአስተዳደር ስርዓት...........................................................28

4.4. የካፋ ብሔረሰብ ባህላዊ ዕምነቶች ..................................................................30

4.5. የአየር ንብረት ሁኔታና ምርቶች .....................................................................31

ምዕራፍ አምስት...................................................................................................32

የመረጃ ትንተና....................................................................................................32

5.1. ግራኝነት ከፍትህ አሰጣጥና ከጠረኝነት አንፃር ያለው ትዕምርትነት.....................32

5.2.ግራኝነት በጋብቻ ስርዓት ውስጥ ያለው ትዕምርትነት.........................................34

5.3. የግራ ትርጉም በእንስሳት አካላት አፈጣጠር ላይ...............................................37

5.4. የግራኝነት እሳቤ በብሐረሰቡ ስነቃል ውስጥ ....................................................38

5.4.1.ግራኝነትና ሚት....................................................................................38

5.4.2.ግራኝ በተብሔረሰቡ ተረት ውስጥ...............................................................40

5.4.3. የግራኝነት እሳቤ በብሔረሰቡ ምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ ..............................42

5.5. የግራኝነትና ከእምነትና ወደፊት ዕድል ትንቢያ አንፃር ....................................44
5.6. ግራኝነት በግብይት ሂደት ውስጥ ያለው ትዕምርትነት ........................................47
5.7. ግራኝነት በአመጋገብ ስርዓት ውስጥ ያለው ትዕምርትነት ..................................48
5.8. ልጆች ግራኝ እንዳይሆኑ የሚደረግ ክልከላ ........................................................49
5.9. ግራኝነት በስነልቡና ላይ የሚኖረው አንድምታ ...................................................50
5.10. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ..........................................................................................52
ምዕራፍ ስድስት ...........................................................................................................55
ማጠቃለያና አስተያየት ..................................................................................................55
6.1. ማጠቃለያ ..................................................................................................................55
6.2. አስተያየት .................................................................................................................56
አባሪ .................................................................................................................................62

ምስጋና

በመጀመሪያ ከትልመ ጥናት አንስቶ ዋናውን ጥናት ያለመታከት በማንበብና ገንቢ አስተያየት በመስጠት፤ የተለያዩ የንድፈ ሀሳብ ዕይታ አድማሶችን በማስፋት ጥናታዊ ፅሑፉ ተቃንቶ በዚህ ደረጃ እንዲቀርብ ላደረጉልኝ፤ እንዲሁም አባታዊ ምክር በመለገስ የመንፈስ ብርታት ለሆኑኝ አማካሪዎቼ አማካሪዬ ለማ ንጋቱን (ዶ/ር) እና ጥበቡ ሽቴን (ዶ/ር) ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ጥናቱን እንዳካሂድ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመግዛት፣ በሀሳብና በሞራል ዘወትር ድጋፍ በመሆን እስከመጨረሻዋ ስራ ድረስ ከጎኔ ላልተለዩኝ ባለቤቴ ወ/ሮ መሰረት ጌታቸውንና ወንድሜ ፅኑኤል አሸናፊን፣ ጊዜዋን መስዕዋት በማድረግ የእርምት ሀሳብ ለለገሰችኝ መ/ርት ውብነሽ ወንድሙን አመሰግናለሁ ፡፡ በመጨረሻም በመረጃ ስብሰባ ወቅት መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት ከቦታ ቦታ በምንቀሳቀስበት ወቅት ከልክ ያለፈ ወጪ ውስጥ እንዳልገባ በትራንስፖርት ረገድ ለተባበረኝ አቶ ታደለ ብርሃኑን፣ የመረጃ አቀባዮችን መኖሪያ ቤት በመጠቆምና ከመረጃ አቀባዮች ጋር ጥብቅ ግብብነት እንድፈጥር ለተባበሩኝ መምህር አድማሱ ወልዴንና መምህር ውብሸት ብርሃኑን እንዲሁም መላው መረጃ አቀባዮቼን ከልብ አመስናግናለሁ፡፡

# የካፊኛ ቃላት አቻ የአማርኛ ትርጉም

1. Iraashoo ኢራሾ ወታደር ወይም የጦር መሪ
2. qaro ቃሮ ጥንድ፣ ተጣማጅ ወይም ቀንበር በጋራ የሚስብ በሬ
3. Qoobeeboo ቆቤቦ ከፈረስ ሾከና ከፍ ብላ የምትገኝ ቀለበት መሳይ ክብ ነጭ መስመር
4. Giifoo ጊፎ ከቀርከሃ የተሰራ ሳጠራ መሳይ የቤት መዝጊያ በር
5. Keepho ኬጶ ሙጃ ወይም ለስላሳ ሳር

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ ‹‹ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ያለውን ማህበራዊ ፍልስፍና (ትዕምርትነት) መተንተን›› ነው፡፡ የጥናቱ ዘዴ አይታዊ ሲሆን የመተንተኛ ስልቱ ደግሞ ገላጭ ትዕምርታዊ ፍከራን የተከተለ ነው፡፡ በታላሚና በጠቋሚ ከተመረጡ መረጃ አቀባዮች አስፈላጊውን መረጃ በቃለመጠይቅና በሰነድ ፍተሻ፣ መቅረፀ ድምፅና ማስታወሻ ደብተር መረጃ መቅረጫ መሳሪያዎችን በመጠቀም መረጃው ተሰብስቧል፡፡ ጥናቱ በካፋ ብሔረሰብ በቦንጋ ዙሪያ፣ በጠሎ እና ዴቻ ወረዳዎች ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የተሰራ ነው፡፡ ከመስክ የተሰበሰበው መረጃ ላይ በተደረገው ትንተናም መሰረት ግራኝነት የሰይጣንነት፣ የክፋት፣ የስግብግብነት ወይም የአልጠግብ ባይነት እንዲሁም በብሔረሰቡ ዘንድ በሚታመኑ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች አንፃር የእርኩስነት ትዕምርትነት ያለው መሆኑ ተመላክቷል፡፡ ሚት ውስጥ ግራኝነት የሰይጣን፣ በተረት ውስጥ ግራ የስውር ተንኮል፣ በምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ የአቅመቢስነት ወይም የአለመታመንና የርኩስ ወይም የመናቅ እንዲሁም በፈሊጣዊ አነጋገር ውስጥ ደግሞ በኢ-ፍትሃዊነት ትዕምርትነት መቅረቡ ተገልጿል፣ ማህበረሰቡ ግራኝነትን በመጥፎ ተምሳሌትነት ወይም ትዕምርትነት እንዲወክል ተፅዕኖ እንዲኖር በዋናነት ያስቻሉት ስነቃዊ እሴቶችና የሀገረሰባዊ ዕምነት አስተምህሮ ተፅዕኖዎች እንደሆኑ፣ ህፃናት ግራኝ እንዳይሆኑ ጥብቅ ክትትልና ግራኝ ከሆኑ የከፋ ቅጣት እስከማስከተል እንደሚደርስ፣ ቅጣቱ በታደጊዎች ስነልቦና ላይ የሚያሳድረው ጫና ቀላል አለመሆኑና በተዛማጅ ጥናት ላይ የተዳሰሱ ጥናቶች ከስነቃል፣ ከሀገረሰባዊ ዕምነት ትዕምርትነት አንፃር ያልዳሰሱትን ጉዳዮች ወይም ክፍተቶች ለመሙላት የሚያስችሉ ነጥቦችን አመላክቷል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ዘሪሁን (2015፣467) ‹‹ባህል በአንድ ማህበራዊ ቡድን፣ ብሔረሰብ ወይም ሀገር በሚመሩ ሰዎች ተቀባይነት አግኝተው ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ ማህበራዊ እሴቶችን፣ ጠባዮችን፣ እምነቶችን፣ የአኗኗር ዘይቤዎችን፣ ሰዎች በአካባቢያቸው በተፈጥሮ ውስጥ ለመኖር የሚጠቀሙባቸውንና በእጃቸው የሰሯቸውን ቁሶችን፣ የኪነጥበብ ስራዎችን ያካትታል፡፡›› በማለት ፎክሎር በውስጡ የሚይዛቸውን አበይት ርዕሰ ጉዳዮች በመጥቀስ ይበይኑታል፡፡ የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት ወይም ርዕስ የግራኝነት ማህበራዊና እምነታዊ ፍልስፍና ትንተና በካፋ ብሔረሰብ ተተኳሪነት ላይ በመሆኑ ከፎክሎር ዘውግ አንፃር ሲታይ ከሀገረሰባዊ ልማድ በንዑስነት ደረጃ ከሀገረሰባዊ እምነት ስር የሚመዘዝ ነው፡፡

ይህ ጥናት በዋናነት ስድስት ምዕራፎችን በውስጡ  የያዘ ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ መግቢያ ስር የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ፣ የጥናቱ ዓላማ ፣ የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰንና የመስክ ተሞክሮ  የሚሉ ንዑሳን ርዕሶች ከተለያዩ ጥናቶችና የምሁራን እሳቤዎች አንፃር ተዳሰው ቀርበዋል ፡፡ በምዕራፍ ሁለት ስር ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝት፣ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝትና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የሚሉ ሶስት ንዑሳን  ርዕሰ ጉዳዮች የቀረቡ ሲሆን በምዕራፍ ሶስት የጥናቱ አካሄድና የጥናቱ ዘዴ፣ የንሞና ዘዴ፣ የመጃ መቅረጫ መሳሪያዎች፣ የመረጃ አደረጃጀት፣ የመረጃ መተንተኛ ስልትና የሙያ ስነምግባር የሚሉ ነጥቦች ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ አራት የጥናቱ አካባቢያው ዳራ ከተለያዩ ነጥቦች አፃር ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ አምስት ከመስክ የተሰበሰበው መረጃ ‹‹የመረጃ ትንተና›› በሚል ርዕስ ቀርቧል፡፡ የመጨረሻው ምዕራፍ ስድስት  ሲሆን የማጠቃለያና አስተያየት ሀሳቦችን ይዟል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ፎክሎርን በዘውግ በመከፋፈሉ ሂደት አንድን የፎክሎር ቅንጣት በአንድ ዘውግ ስር ለመመደብ አንዳች የጋራ ጉዳይ አስፈላጊ እንደሆነ እሙን ነው፡፡ በመሆኑም የተለያዩ የዘርፉ ምሁራን የተለያዩ የጋራ ጉዳዮችን በማንሳት የፎክሎር ዘውጎችን በተለያዩ ክፍሎች ሲመድቡ ይታያሉ፡፡ አንዳንድ ምሁራን እንደነ Tollken(1996) ያሉ ‹‹ፎክሎር ዘውጎች ሶስት ናቸው›› በማለት ሶስቱን ምድቦች ይዘረዝራሉ፡፡ ሌሎች እንደነ Dorsen(1972) ያሉ ደግሞ ‹‹የፎክሎር ዘውጎች በዋናነት አራት ናቸው›› በማለት አራቱን ይዘረዝራሉ፡፡ ስነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በማለትም ይዘረዝሯቸዋል፡፡ በውስጣቸውም የተለያዩ ንዑሳን የፎክሎር ቅንጣቶችን ይመድባሉ፡፡

ፍቃደ (1991፣13) ዶርሰንን በመጥቀስ ሀገረሰባዊ ልማድ በሚለው ክፍል ውስጥ አራት አበይት ርዕሰ ነገሮችን እንደሚገኙ እነርሱም ‹‹ፌስቲቫልና ክብረ በዓል (ከበራ)፣ (Festivals and Celebrations)፣ መዝናኛዎችና መጫዎቻዎች (Recreations and games)፣ ሀገረሰባዊ መድሃኒት (Folk medicines) እና ሀገረሰባዊ ሃይማኖት (Folk relision) ናቸው›› በማለት በሀገረሰባዊ ልማድ ስር የሚካተቱ ንዑሳን ርዕሶችን ይገልፃሉ፡፡

ሀገረሰባዊ እምነት ወደፊት እንዲሆኑልን ከምንፈልጋቸው ወይም ሊከሰቱብን ከማንፈልጋቸው ውጤቶች በመነሳት ከተግባራዊ ምክሮች፣ ከድርጊቶችና ከጥንቃቄ፣ ለመፈወስና ከመሳሰሉት ከዕለት ተዕለት ድርጊቶች አንስቶ ስለምናየው ተፈጥሯዊው ዓለም እንዲሁም ስለማይታዩት ምናባዊ ዓለማት ያለንን እይታ የማሳወቅ ሂደት ድረስ ያሉ መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦችን የሚይዝ የፎክሎር ዘውግ ነው፡፡ ሀገረሰባዊ እምነት ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮችን ይይዛል፡፡ እነሱም አማኙ፣ የሚታመነው ነገርና በአማኙና በሚታመነው ነገር መካከል ያለው የማመን ሂደት ነው (ሰሎሞን 2007፣180)፡፡

ከላይ የቀረቡትን የፎክሎር ዘውጎች ትስስር ማንሳቱ በዋናነት ያስፈለገበት ምክንያት የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት የግራኝነት ማህበራዊና እምነታዊ ትዕምርትነት ትርጓሜ ወይም ፍልስፍና በካፋ ብሔረሰብና በብሔረሰብ ስነቃሎች ላይ ትንተና ማካሄድ በመሆኑ እንዲህ አይነት እሳቤ ከሀገረሰባዊ እምነቶች ስር ከ‹‹ሚልኪ›› ንዑስ ርዕስ የሚካተት በመሆኑ ነው፡፡

Alhassan (2017) ‹‹Left Handedness, The Bible and The Qur'an: Implications for Parents and Teachers›› በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ዋነኛ ትኩረቱ ግራ እና ቀኝ የአካል ክፍሎች ወይም ግራና ቀኝ እጅ በመፅሐፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁርአን ምን ያህል ጊዜና በምን አይነት መልኩ ማለትም የትኛው በአዎንታዊ የትኛው በአሉታዊ ሁኔታ እንደቀረበና ተማሪዎች ወይም ልጆች በግራ የመፃፍና የመስራት ክልከላ በሚደርስባቸው ወቅት የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በመተንተን አሳይቷል፡፡

Jennifer (2006) ‹‹psychosocial differences between left-handed and Right handed children›› በሚለው ጥናቷ በዋናነት ግራኝ መሆን በልምምድ ማለትም በልጅነት ጊዜ በአምስት አመታቸው ተግባራትን ለማከናወን የእጅ መረጣ የሚያካሂዱበት ወቅት በመሆኑ በዚያ የዕድሜ ክልል በተደጋጋሚ በሚከውኑት እጅ ለምደው እንደሚቀሩ በማመላከት ከቀኞች ይልቅ ግራኞች ከስነልቦና አንፃር ዝቅተኛ አመለካከት (self concept) እንዳላቸው፣ ከፍተኛ የድብርት ስሜት የሚጫጫናቸው መሆኑንና ውጫዊ ክትትል የሚያሻቸው መሆኑን አመላክታለች፡፡

Iris እና René (2009) ‹‹The history and geography of human handedness›› በሚለው ጥናታቸው ግራኝነትን ከታሪካዊ ዳራና መልካዓ ምድራዊ አቀማመጥ መነሻነት ልዩነትን እንደሚፈጥርና የማህበረሰቡ ተፅዕኖ በእጅ ምርጫ ላይ የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳለው ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም የሰው ልጆች ቋንቋን ለመልመድ አንዳንዶቹ ግራ የአዕምሮ ክፍላቸውን የሚጠቀሙ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ቀኝ የአዕምሮ ክፍላቸውን እንደሚጠቀሙና ይህም ልዩነት ከታሪካዊና መልካዓ ምድራዊ ተፅዕኖ እንደሚመነጭ ያስረዳሉ፡፡

ከላይ የተዳሰሱት ጥናቶች በዋናነት ግራኝነትን ከስነልቦናና ከሀይማኖት እሳቤ አንፃር ትንተና የሚሰጡ በመሆናቸው በማህበራዊ አውድ ውስጥ ከሀገረሰባዊ እምነት አንፃር ማህበረሰቡ ለግራኝነት የሰጠውን ትዕምርትነት ከመተርጎምና ከማህበረሰቡ ስነቃል አንፃር የማይተነትን በመሆናቸው ጉልህ ክፍተት ይታይባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ግራኝነት ወይም ግራ እጃቸውን የሚጠቀሙ ሰዎች በአንፃራዊነት ሲታዩ ቁጥራቸው ጥቂት ሲሆን ግራኝነት በማህበረሰቡ ዘንድ አሉታዊ አመለካከት እንዳለውና ግራኝነት በአካባቢው ማህበረሰብ ተጽዕኖ እንዲሁም እጆች ተግባርን በሚለምዱበት የዕድሜ ወቅት አንዱ ላይ ብቻ (ግራ ወይም ቀኝ) ያተኮረ ልምምድ ማድረግ በዕደገት ወቅት

የግራኝነትን ወይም የቀኝነትን ዕጣ ፋንታ እንደሚወስን ያመላክታሉ፡፡ ከህገረሰባዊ እምነት አንፃር፣ በስነቃላዊ ዘውግ ውስጥ ግራኝነት የተሰጠውን ትረጓሜና ትዕምርትነት በጥናታቸው ትንተና ያልታዳሰሰ በመሆኑ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ከአጥኚው ከ2008 ዓ.ም - 2010ዓ.ም በካፋ ዞን ጠሎ ወረዳ በመምህርነት ሙያ ተቀጥሮ ሲሰራ በ21/05/2009ዓ.ም ሚዜ በመሆን ሰርግ ላይ በተሳተፈበት ወቅት በስጦታ መልክ የቀረበውን የ‹‹ውስኪ›› መጠጥ ለሁሉም ታዳሚዎች ሳያደርስ ፊት ላሉት ብቻ በመስጠት ይጨርሰዋል፡፡ በዚህን ጊዜ መጠጡ ያልደረሳቸው ታዳሚዎች በጭፈራ ወቅት ‹‹የግራ ሚዜ ፊዞ ደንዝዞ ይቅር፣ በግራ እየቀዳ ከዳር ሳይደርስ ይቅር›› በማለት በስነቃላቸው ይወርፉታል፡፡ ለመወረፉ ዋነኛ ምክንያት መጠጡን ያለማድረሱ ብቻ ሳይሆን ሚዜው በግራ እጅ ስለሚቀዳም ነበር፡፡ በካፋ ብሔረሰብ ጋብቻ ወቅት ሚዜዎች የግራና የቀኝ ተብለው ይወከላሉ፡፡ በብሔረሰቡ አመለካከት ከግራ ሚዜ ይልቅ የቀኝ ሚዜ ተአማኒነት አለው፡፡ ግራኙ ሚዜ ከቀኙ እኩል በብሔረሰቡ ዘንድ ያለመታመኑና የግል ገጠመኙ ምክንያት ከምን የመነጨ እንደሆነ የማጥናት ውስጣዊ ፍላጎት ተቀደሚው ምክንያት ነው፡፡ ሁለተኛ የካፋ ብሔረሰብ የግራኝነትን በተለያዩ ትዕምርት ወክሎ ያሳያል፡፡ በአብዛኛው ትዕምርቶቹ ከአሉታዊነት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ብሔረሰቡ ግራኝነት በአሉታዊነትም ሆነ በአዎንታዊነት የሚገልፅበት ሂደት ማህበራዊ ፍልስፍና ላይ  ወይም ዕምነታዊ አስተምህሮ ላይ የተመረኮዘ መሆኑን የማጥናት ከፍተኛ የውስጣዊ ጉጉት ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተዳሰሱት ጥናታዊ ፅሑፎች ላይ ግራኝነት በብሔረሰቡ ውስጥ ያለውን ትዕምርትነትና በስነቃል ውስጥ የቀረበበትን መንገድ የመተንተን ክፍተት ይታይባቸዋል፡፡ ይህንን አካዳሚያዊ ክፍተት የመሙላት ፍላጎትም ተጠቃሽ ነው፡፡

በሶስተኛነት ብሔረሰቡ ‹‹ይህንን በግራ አታድርግ፡፡›› በማለት ክልከላዎችን ያስቀምጣል፡፡ ‹‹ለምን?›› የሚል ጥያቄ ሲቀርብ የሚሰጡት ምላሽ ከማህበራዊ ፍልስፍናቸው አንፃር ምን እንደሚመስል በመተንተን የማቅረብ ውስጣዊ ፍላጎት ተጠቃሽ ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ያለውን ማህበራዊ ፍልስፍና (ትዕምርትነት) መተንተን ነው፡፡ ንዑሳን ዓላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ያለውን ትዕምርትነት በግልፅ ተንትኖ ያቀርባል፡፡
- የግራኝነት ክልከላ መሰረቶችን ያብራራል፡፡
- ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ስነቃል ውስጥ የተገለፀበትን መንገድ ይተነትናል፡፡
- በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ግራኝነት ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ አንድምታ ይገልፃል፡፡ የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ለሚከተሉት ጥያቄዎች አስፈላጊውን ምላሽ ለመስጠት ጥረት አድርጓል፡፡ ጥያቄዎቹም፡-

1. ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ምን አይነት ትዕምርትነት አለው?
2. የግራኝነት ክልከላ መሰረቶች ምንድን ናቸው?
3. ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ስነ ቃሎች ውስጥ እንዴት ተገለፀ?
4. በካፋ ብሔረሰብ የግራኝነት ትዕምርቶች አንደምታ ምን መስላል? የሚሉ ናቸወ፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የካፋ ብሔረሰብ ግራኝነትን የሚገልፅበትን ሁኔታ ወይም ትዕምርትነትን ከባህል አንጻር የሚያመላክት በመሆኑ በብሔረሰቡ ዘንድ ‹‹ይህንን በግራ አታድርግ›› የሚለው ክልከላ ከምን የመነጨ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ በመሆኑም ‹‹ለምን በግራ አይሰራም ወይም አይደረግም?›› ለሚል ማህበራዊም ሆነ ግለሰባዊ ጥያቄ ምላሽ የመስጠት ጠቀሜታ አለው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ውስጥ የቀረበበትን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ገፅታን የሚተነትን በመሆኑ በስነቃሎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ማህበራዊ ተፅዕኖ ዙሪያ እንዲሁም ከግራኝነትና ከሰውነት ክፍሎች ማህበራዊ ትርጓሜ አንፃር ጥናት ለሚያካሄዱ አካላት የመረጃ ምንጭ የመሆን ጠቀሜታም አለው፡፡ ጥናቱ ከባህልና ከብሔረሰቡ ስነቃል ጋር የተያያዘ በመሆኑ የብሔረሰቡን ባህልና ስነቃል የመቀረስ ወይም የመሰነድ ጠቀሜታ አለው፡፡

ከአካዳሚያዊ አንፃር ጥናቱ ከፎክሎር ዘውጎች ከሀገረሰባዊ ልማድ መነሻ ያደርጋል፡፡ ከሀገረሰባዊ ልማድ ስር ከሀገረሰባዊ እምነት ስር ይመደባል፡፡ በአነስተኛ ቅንጣትነት ሚልኪን በመፈከሪያ ጉዳይነት ያነሳል፡፡ በመሆኑም በፎክሎር ጥናት መስክ ውስጥ ከትልቁ ዘውግ እስከ ክፍል ያለውን ተዛምዶና ትኩረት ያልተሰጣቸውን የፎክሎር ቅንጣቶች ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲጠኑ የማስቻል፤ በተጨማሪም አንደኛው ዘውግ ከሌላኛው ዘውግ ያለውን የትስስር ኃይል (ሀገረሰባዊ እምነትና ስነቃል) የማሳየት ጠቀሜታ አለው፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ሀገረሰባዊ ልማድ በስሩ ወደ አስር የሚጠጉ ንዑሳን ምድቦችን ይይዛል፡፡ ከዚህ መካከል አንዱ ሀገረሰባዊ እምነት ነው፡፡ በሀገረሰባዊ እምነትም በርካታ ንዑሳን ዘውጎች በውስጡ ይገኛሉ፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከሚልኪ ጋር ተያያዥነት ያለው ግራና የአካል ክፍሎችን መሰረት በማድረግ የሚተነበዩ አዎንታዊና አሉታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ሲሆን አጠቃላይ ሀገረሰባዊ ልማዶችንና እምነቶችን ሙሉ በሙሉ አልዳሰሰም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የካፋ ብሔረሰብ የበርካታ ስነቃላዊ፣ ቁሳዊ፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ባለቤት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እያንዳንዱን የፎክሎር ዘውግ መተንተን አዳጋች በመሆኑ ብሔረሰቡ ከግራኘነት ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ የሚያነሳቸው ጉዳዮች በብዛት ሀገረሰባዊ እምነት ሚልኪና ስነቃላዊ ሀብቶች ላይ የሚገኝ በመሆኑ በሚት፣ በተረት፣ በምሳሌያዊ አነጋገርና በፈሊጣዊ አነጋገር ላይ ብቻ ትኩረት አድርጓል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ከቦታ መረጣ አንፃር በካፋ ዞን ውስጥ አስራ ሁለት ወረዳዎች ያሉ ሲሆን ይህ ጥናት በዋናነት ትኩረት ያደረገው ጠሎና ዴቻ ወረዳዎች እንዲሁም በዞኑ ዋና ከተማ ቦንጋ አካባቢ ላይ ነው፡፡ ሌሎች አስር ወረዳዎችንና አንድ ከተማ አስተዳደርን አያካትትም፡፡ ከጠሎ ወረዳ ሃያ አምስት ቀበሌዎች መካከል ትኩረት የተደረገባቸው የገባላና ኦዳ ቀበሌዎች ሲሆኑ ሌሎች ሃያ ሶስት ቀበሌዎች በጥናቱ አልተካተቱም፡፡ በአንፃሩ ከዴቻ ወረዳ አውራዳና ፍቅረ ሰላም ቀበሌዎች የተመረጡ ሲሆን እነኚህ ቦታዎች በዋናነት የተመረጡበት ምክንያትም አስፈላጊውን መረጃ የሚሰጡ መረጃ አቀባዮች ማለትም በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ እውቅና ያላቸው ታሪክና ባህል አዋቂ መረጃ አቀባዮች ያሉባቸው በመሆናቸውና ከሌሎች ወረዳዎች በአንፃራዊነት የስነቃል ዕውቀት ያላቸው

(አቀንቃኞች ለማግኘት አመቺ ወረዳዎችና ቀበበሌዎች በመሆናቸው መረጃዎችን በተገቢው መንገድ መሰብሰብ እንዲቻል በዓላማ ተኮር የተመረጡ ናቸው፡፡

## 1.7. የመስክ ተሞክሮ

አጥኚው ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከቦንጋ፣ ከጠሎ እና ከዴቻ ወረዳዎች በስፋት ቃለመጠይቅን በመጠቀም ሰብቧል፡፡ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ከእየአካባቢው የመረጃ አቀባዮችን ማንነት የሚያውቁ ሰዎችን መረጃ አቀባዮች ጋር ይዞ መቅረቡ በአጥኚውና በመረጃ አቀባዮች መካከል ጥብቅ የሆነ ግብብነት እንዲፈጠር አስችሏል፡፡ በቃለመጠይቅ ወቅት የጥናቱ እና የመሪ ጥያቄዎች አዲስ መሆን መረጃ አቀባዮችን ግራ እንዲጋቡ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህ ወቅትም አጥኚው ጥያቄዎችን ወደአካበቢዊ አውድ በመለወጥ ማለትም ‹‹የካፋ ብሔረሰብ ግራኝነትን እንዴት ይገልፀዋል?›› የሚለውን መሪ ጥያቄ ‹‹ በግራ ገንዘብ ለሰው የማይሰጠውና በግራ በር የማይከፈተው ለምንድንነው?›› በማለትና በሳሰሉት ስልት ችግሮችን በመቅረፍ መረጃውን ሰብስቧል፡፡

ግራኝነትን መሰረት ያደረጉ ስነቃላዊ መረጃዎች ማለትም ሚት፣ ተረት፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ሌሎችን መረጃ አቀባዮች በሚጠይቁበት ወቅት ወዲያው አለማስታወስ የመረጃ መስብሰቢያና መተንተኛ ጊዜው እንዲራዝም አድርጎታል፡፡ አጥኚውም ተዳጋጋሚ መመላለስ (ምልልስ) በማድረግና በሰነድ በመፈተሽ ከመፃሕፍት ያገኛቸውን መረጃዎች እንደማሳየነት ለመረጃ አቀባዮች በማንሳት ከአንዳንድ መረጃ አቀባዮች ስነቃላዊ መረጃዎች በመሰብሰብ ትንተናውን አካሂዷል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1. የፎክሎር ምንነት

ፎክሎር የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በአንዳች የመሰብሰቢያ ምክንያት በመሰባሰብ በተሰበሰቡበት ሎር አማካይት አንዳች ተግባር የሚፈፅሙበት ሲሆን የሚፈፅሙትም ተግባር የማህበረሰቦችን የተለያየ ገፅታ ማለትም ባህል፣ ልማድ፣ የአኗኗር ዘይቤ…ወዘተ. የሚያንፀባርቅ ነዉ፡፡

ፎክሎር የተለመደ ነባር እምነት፣ ልማድና አገላለፅ አካል ነዉ፡፡ ተስተላልፎዉም በአብዛኛዉ በቃል ሲሆን፣ ከንግድ፣ ከትምህርትና ከተቋማት ተግባቦታዊና ትዕዛዛዊ ትርጓሜ ዉጪ ነዉ፡፡ በአንድ አካባቢ ያለ ማንኛዉም ቡድን አንድ የሚያገናኘዉ የራሱ የሆነ ፍላጎትና ዓላማ አለዉ፡፡ ይህንን የልማድ አካል ፎክሎር ብለን ልንጠራዉ እንችላለን፡፡ በእነዚህ ነባር ልማዶችም ዉስጥም የተለያዩ አላባውያንና ግለሰቦች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን ሁሉም በድግግሞሹና በልዩነቱ ተውጠውና ተመሳስለው ለቡድኑ የጋራ እሴትና ቡድኑ ለሚኖረው ቀጣይነት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ (ሰሎሞን፤2007፣ 13)፡፡

ከገለፃው ፎክሎር የአንድ ማህበረሰብ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እሳቤዎች መገለጫ መሆኑን፤ አንድን ማህበረሰብ እርስበርስ የማስተሳሰር አቅም ያለውና የማህበረሰቡ የጋራ ስምምነት ደንብ እንደሆነና ሁለቱ ተነጣጥለው የማይታዩ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

የፎክሎር የጥናት ዘርፎችን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መክፈል ይቻላል፡፡ እነዚህ አራት ዋና ዋና ክፍሎች ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ቁሳዊ ባህልና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ሲሆኑ እያንዳንዳቸው በስራቸው በርካታ ንዑሳን የጥናት ዘርፎችን የያዙ መሆናቸዉን (ፈቃደ፤1991፡10) ይገልፃሉ፡፡

ስነቃል የልዩ ልዩ ቅርፆች ጥቅል መጠሪያ ሲሆን በውስጡም ተረቶችን፣ ሐተታ ተፈጥሮዎችን፣ አፈታሪኮችን፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ እንቆቅልሾችን፣ እንካሰላንቲያዎችን፣ ቃል ግጥሞችንና የመሳሰሉትን በቃል አማካይነት የሚገለጹትን ጥበቦችና እነሱን የሚያጠናውን ሙያ የሚያጠቃልል ነው (Ben Amos 1982፣ 291)፡፡

ቁሳዊ ባህል በዓይን የሚታየውን፣ በእጅ የሚዳሰሰውን ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ መስፋፋት በፊት አንስቶ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ፣ የልዩ ልዩ ባህላዊ ምግቦች አሰራርን፣ የልብስን፣ የቤትና የአጥር አሰራርን፣ ሰዎች ስራ የሚያከናውኑባቸውን ባህላዊ መሳሪያዎችና ሌሎችም መሰል ነገሮችን ያጠቃልላል (ፈቃደ 1991፣ 15)፡፡

Setephen (2011፣ 2) ፎክሎር ከአንትሮፖሎጂና ከስነፅሑፍ ጥናት አንፃር ሊጠና የሚችል እንጂ የአንትሮፖሎጂ ወይም የስነፅሑፍ ሌላኛው ገፅታ ሳይሆን እራሱን የቻለ የጥናት መስክ ነው፡፡ ስነልቦናዊና ሶሾሎጂ ጥናት መስኮችም ጥናት የሚሆኑ ነጥቦችን የያዘ ነው፡፡ ፎክሎር የራሱ የሆነ የጥናት ድስፕሊን ያለው ነው፡፡ በማለት ይገልፀዋል፡፡

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በዚህ ጥቅል መጠሪያ የሚካተቱት ደግሞ ሐገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ሐገረሰባዊ ዳንስና ሐገረሰባዊ ድራማ ሲሆኑ ስሙ እነዚህን ለሚያጠናው የሙያ መስክ መጠሪያነት ጭምር ያገለግላል፡፡ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የሐገረሰብ ልብስ ተለብሶ፣ በሐገረሰብ ሙዚቃ መሳሪያዎች ታጅቦ፣ አስፈላጊው መኳኳልና መጊያጊያጥ ከተደረገ በኋላ የሚከወነውን ሁሉ ይመለከታል (ፈቃደ 1991፣ 12)፡፡

ይህ ጥናት ከላይ ከተጠቀሱት የፎክሎር ዘውጎች በተጨማሪ ሀገረሰባዊ ልማድ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ከሀገረሰባዊ ልማድ ስር ከሚመደቡት አራት አብይ ክፍሎች መካከል ሀገረሰባዊ እምነት ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ሀገረሰባዊ ልማድንና ሀገረሰባዊ እምነትን መሰረት ያደረጉ ትንተናዎች እምደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 2.1.2. የሀገረሰባዊ ልማድ ምንነት

የባህል ጥናት ከሚያተኩርባቸው ሰዋዊ ተግባራት መካከል አንዱ ማህበራዊ ልማዶች ናቸው፡፡ ማህበራዊ ልማዶች ማህበረሰቡ ወቅት እየጠበቀ የሚያደርጋቸው ክበረ በአላት፣ ልዩ ልዩ ጨዋታዎችና የተዝናኖት ተግባራት፣ ሀገረ ሰባዊ መድሀኒት፣ እና ሀገረሰባዊ ሀይማኖቶች ናቸው፡፡ በክብረ በዓላቱ ላይ የሚፈጸሙ ስነ ስርአቶች ጸሎቶች፣ ዝማሬዎች፣

ልዩ ክዋኔዎች ይጠናሉ፡፡ ከዕፅዋት፣ ከማዕድናትና ከእንስሳት የሚገኙ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች አዘገጃጀት፣ አሰጣጥ አጠቃቀም እንዲሁም ከመድሀኒቶቹ ጋር የተያያዙ እምነቶች ይጠናሉ፡፡ በማህበረ ሰቡ ውስጥ ከልጆች እስከ አዋቂዎች ለመዝናናት የሚያደርጓቸው ልዩ ልዩ ጨዋታዎችም በማህበራዊ ልማድነታቸው የጥናት ትኩረት ይሰጣቸዋል (ዘሪሁን 2015፣ 473)፡፡

Dorsen (1972፣3-4) በሀገረሰባዊ ልማድ ዘዉግ ስር የሚካተቱት የፎክሎር አይነቶችን በአራት ይመድባቸዋል፡፡ እነሱም ፌስቲቫሎችና ክብረ በዓላት፣ መዝናኛዎችና ዉድድራዊ ጨዋታዎች ሀገረሰባዊ መድሃኒትና ሀገረሰባዊ ህይማኖት ናቸዉ፡፡

ከዚህ መረዳት የምንችለው ነገር ሀገረሰባዊ ልማድ በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመደና የተዘወተረ ማህበረሰቡ የቀጣይነት ህልውናውን ያረጋግጥልኛል በማለት በመደጋገም የሚከውነው ተግባርና በማህበረሰቡ ዘንድም ስር የሰደደ ተግባር መሆኑን ነው፡፡ በተለመደ መልኩ ማህበረሰቡ ይከውነዋል፤ ለመጪው ትውልድም ልማዳዊ ድርጊቱን ከእነተግባሩና ከነአከዋወን ስርዓቱ ጋር ያስተላልፈዋል፡፡ ሀገረሰባዊ ልማድ በስሩ ከያዛቸው ዘርፎች መካከል ሀገረሰባዊ እምነት በተመሳሳይ መልኩ በስሩ በርካታ ዘርፎችን ይይዛል፡፡

### 2.1.2.1. ትዕምርት (symbol)

ትእምርት የምንለው በአንድ ማህበረሰብ ዘንድ በውክልና የሚገልጸውን ሲሆን ማህበረሰብ በባህሉ ውስጥ የሚገኙት ትምህርቶች እራሳቸውን ወይም በተለያዩ አውዶች በሚከወኑ ስርዓተ ከበራዎች፣ ክብረ በዓሎች፣ ዘፈኖች ወዘተ ውስጥ ማህበራዊና ባህላዊ ትርጓሜ ይዘው ይገኛሉ (ጣሂር 2011፣ 34፡፡)

እያንዳንዱ ማህበረሰብ መልካምነትና ክፋትን፣ እድለኝነትንና እድለቢስነትን በተለያዩ ነገሮች ወክለው ለወከሉት ነገር ማህበራዊ አንደምታ ያለው ትዕምርትነት ይሰጣሉ፡፡ የትዕምርት አሰጣጥ ሂደቱና የትዕምርቱ ትርጓሜ ከብሔረሰብ ብሔረሰብ፣ በማህበረሰብ ማህበረሰብ እንዲሁም ከሀገር ሀገር የተለያየ ነው፡፡ ለአብነት ያህል በሀገራችን ነጭ ልብስ መልበስ የደስታ መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በአንፃሩ በህንድ ሀገር ደግሞ የሀዘን መገለጫ ትዕምርትነት አለው፡፡ በመሆኑም ከክፋትና መልካምነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በሚልኪ ስር የሚጠኑ ናቸው፡፡

### 2.1.2.2 ሚልኪ

ሚልኪ በማህበረሰቡ ውስጥ ወደፊት ክፉ ነገር ወይም መጥፎ አጋጣሚ ይከሰታል በሚል እምነት የማይከወኑና እንዳይከሰቱ የሚፈለጉ ድርጊቶችና ትዕምርቶች አሉ፡፡ የማህበረሰቡ አባላት እነዚህ ድርጊቶችና ትዕምርቶች ቢከሰቱ በማህበረሰቡ ባህል ውስጥ ያላቸውን ትዕምርት መሰረት በማድረግ ወደፊት አንድ ችግር ያጋጥማል በማለት የሚያምንባቸው ሀገረሰባዊ እምነቶች ሚልኪ ይባላሉ፡፡ የሚልኪ ሀገረሰባዊ እምነት አመልካች ድርጊቶችና ትዕምርቶችን የሚያሳዩ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ቀጥለን እንመልከት፡፡

> ጠዋት ከመኝታ በግራ ጎን መነሳት፣ ቀኑ ጥሩ ያልሆነና አንድ ክፉ ነገር እንደሚገጥም ማመን፡፡ ወደመንገድ ስንሄድ ከፊት ለፊት መንገዳችንን ቀበሮ ወይም ጥቁር ድመት ቢያቋርጥ የምንሄድበት ጉዳይ የማይሳካና መጥፎ ነገር እንደሚገጥመን ማመን፡፡ ወደመንገድ ስንሄድ ባዶ እንስራ የተሸከመች ሴት ወይም ባዶ አቆማዳ የተሸከመ አህያ ካጋጠመን የምንሄድበት ጉዳይ አይቀናም ብሎ ማመን፡፡….›› (ሰሎሞን፤ 2007፣ 184)

ሀገረሰባዊ ልማድን፣ ሀገረሰባዊ ዕምነትንና ሚልኪን በዋናነት ትኩረት አድርጎ ማንሳቱ በዋናነት የፎክሎሮች ቅንጣት እርስ በርሳዊ ትስስርን የሚያሳይ ሲሆን ጥናቱ በዋናነት ከግራኝነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከፎክሎር ዘውግ አንፃር የግራኝነት ዕሳቤ ወይም ትዕምርትነት በየትኛው ስር እንደሚጠና ለማመላከት ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም የካፋ ማህበረሰብ ግራኘነትን ወደፊት ከሚገጥመው ነገር ጋር የማማያዝ ወይም አንዳንድ ተግባራት በግራ እጅ ወይም ጎን ቢተገበር ማህበረሰቡ ምን አይነት ግብረ መልስ ሊኖረው እንደሚችል ለማመላከት ከሚልኪ አንፃር መፈከሩ ተገቢ ነው፡፡

## 2.1.2. የግራኝና ግራኝነት ብያኔ

‹‹ግራ›› የሚለውን ቃል የተለያዩ ሀይማኖታዊም ሆኑ ዓለማዊ መጻሕፍት ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ይተረጉሙታል፡፡ በመሆኑም ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት መፅሐፍ (1951፣ 2106) ‹‹ግራ›› የሚለውን ቃል ‹‹በግራ የሆነ ነገር፣ ግራ እጅ፣ ግራ እግር ወይም ክፉና ቅን ነገርን ያልሆነውን አመልካች ነው›› በማለት ይገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የመፅሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1972፣ 246) ‹‹ግራ›› የሚለውን ቃል ‹‹የቀኝ

ተቃራኒ፣ አንዳንድ ጊዜ ግራ የክብር ምሳሌነት ቢኖረውም እንደ ቀኝ አይሆንም[1]›› በማለት የቅዱስ መፅሐፍ ጥቅስን በማጣቀስ ይገልፃል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ዕሳቤዎች አንፃር ግራ የሚለው ቃል ከሰውነት ክፍል ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ ያለው ሲሆን የቀኝ ተቃራኒ የሆነ የአካል ክፍል እንደሆነም ያመላክታል፡፡ በመሆኑም ግራ የአካል ክፍል በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ ዕውቅና ያለውና ተመሳሳይነት ያለው የአካል ክፍል ሲሆን በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ዘንድ ግራኝነት ያለው ትዕምርትነት (symbolic) እንደማህበረሰቡ አተያይ የተለያየ ነው፡፡ ግራኝነት ማለትስ ምን ማለት ነው? ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ የግራን ምንነት መበየኑ ብቻ ምላሽ ይሰጣል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በመሆኑም ግራኝነት ከማህበራዊ ትዕምርትነት አንፃር በምን መልኩ እንደሚገለፅም መዳሰስ አስፈላጊ ነው፡፡

‹‹ግራኝ›› የሚለውን ቃል ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት መፅሐፍ ውስጥ (1951፣ 2107) ‹‹በቀኝ እጁ ስራን የማይሰራ፤ በግራ እጁ የሚሰራ ሰው ሁሉ ግራኝ ይባላል፡፡›› ሲል ከግራ ምንነት ጋር የተያያዘ ፍቺ ይሰጣል፡፡ ከዚህ ፍች ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ግራኝነት የሚለውን ቃል የእንግሊዘኛው ‹‹Wikipedia›› እንዲ ሲል ይተረጉመዋል፡፡

> **Left-handedness** is a preference to use the left hand more than the right hand for daily activities such as writing or using tools. Most people can use either hand for many things. However, people very often have a definite preference for using the left or right hand for things such as: using a pen, using a knife, using scissors, brushing teeth, blowing their nose, and so on.

ይህ ብያኔ ሲተረጎም ‹‹ግራኝነት ማለት ግራ እጅን ከቀኝ እጅ ይልቅ ለተለያዩ ተግባራት ማለትም ለፅህፈት፣ ለተለያዩ የመቁረጥ ተግባሮችና ጥርስን ለመቦረሽ ተግባር ግራ እጅን በይበልጥ የመምረጥ ሂደት ነው፡፡›› የሚል ሲሆን ግራ እጅን ለተለያየ ተግባር የመጠቀም ሂደት እንደሆነ ያመላክታል፡፡ ከዚህ ትርጓሜ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ‹‹RXlist›› የተሰኘ ድህረ ገፅ ግራኝነትን እንዲ ይገልፃል፡፡

**Left-handed:** The preferential use of the left hand for most fine manual tasks. Approximately 10% of the population is left-handed. In French, the word for left is gauche meaning clumsy or awkward and the word for right is adroit. In Latin the word for left is sinister and that for right is Dexter (as in dexterity), as left-handed person were historically been seen as abnormal.

**ይህ ብያኔ በዓለም ላይ ምን ያህሉ ህዝብ ግራኝ እንደሆነ በአማካይ በማስቀመጥ ግራኝ መሆን በበርካታ ሀገራት ዘንድ ቀኝ ከመሆን አንፃር ሲታይ በፈረንሳውያን ዘንድ ግራኝ የሆነ ሰው ግራ ወይም ገልጃጃ (የማይመች)፣ በላቲን ግራኝ ማለት ልግመኛ ወይም በጎ ፈቃድ የማያሳይ የሚሉ ትርሜዎች አንዳሉትና በአጠቃላይ ግራኝ መሆንን እንዳለመታደል ወይም የመጥፎ ተምሳሌት አድርገው እንደሚገልፁ ያመላክታል፡፡ ይህ ዕሳቤ የግራኝነትን ትዕምርትነት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ያመላከተ ዕሳቤ ነው፡፡ ከግራኝ እጅ ወይም አካል ማህበራዊ ትዕምርትነት አንፃር** ‹‹THE ENCYCLOPEDIA OF WORLD PROBLEMS& HUMAN POTENTIAL›› **ድህረ ገፅ ግራኝነት ወይም ቀኝ መሆን በማህበረሰቡ ዘንድ ምን አይነት ትዕምርትነት እንዳለው እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡፡**

Symbolic differentiations of left and right are virtually universal cultural classifications among humankind. Left hander's live with a biased vocabulary "Adroit" and "Dexterous" are associated with the right hand, but "sinister" and "gauche" with the left. The righteous sit on the right hand of God. In 1909, French sociologist Robert Hertz made the following observation: "To the right hand go honors, flattering designation, prerogatives; it acts, orders, and takes. The left hand, on the contrary, is despised and reduced to the role of a humble auxiliary; by itself it can do nothing; it helps, it supports, it holds".

Left Contempt for the left hand as compared with the *right is found in most cultures, past and present, and may have arisen simply because most people let its strength and skill remain relatively undeveloped; the English word comes from a root whose primary meaning is 'weak, worthless'. To this basic concept further meanings were added; already in the classical world the left was

unlucky, ominous, and less honorable than the right, while Christianity associated it with moral evil through its description of a Last Judgment where the damned ('goats') are sent to the left, and the saved ('sheep') to the right (Matthew 25: 33).

ከፍ ብሎ የቀረበው ፅሑፍ ሲተረጎም ‹ግራና ቀኝን መሰረት ያደረጉ ትዕምርቶች አካባቢያዊ ብቻ ሳይሆን አለማቀፋዊ ይዘት ያለው ነው፡፡ ‹እነሆ ሰማያት ተከፍተነው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ› (ወደ ሮሜ. 8፣ 34) ተብሎ እንደተጠቀሰው አንዳንድ ማህበረሰቦች ቀኝን ክቡር፣ ለሹመት የተመረጠና የጀግና ተምሳሌት አድርገው ይገልፁታል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ግራን ፣ ከአድሏዊነት፣ ደካማነት፣ ዕድለኛ ካለመሆን፣ ከቀኝ አንፃር ያነሰ ክብር ያለው መሆኑን የእንግሊዘኛው ቃል ግራና ቀኝ መሰረቱ እንደሚያመላክት› ይገልፃል፡፡

ከላይ የቀረበው ፅሑፍ በአጠቃላይ ግራኝነትና ቀኝነት በሁለንተናዊ ደረጃ ትዕምርትነት ያላቸው ሲሆን ይህ ትዕምርትነታቸውም ግራኝነት እንደ መጥፎ እድል ወይም አሰከፊ እንደሆነ እንዲሁም አድሏዊነት ያለው መሆኑን ያመላክታሉ፡፡ ቀኝነት በአንፃሩ በቅዱስ መፅሐፍ እንደተጠቀሰው ‹‹ፃድቃን በእግዚአብሔር ቀኝ ይቀመጣሉ›› እንደሚለው ቀኝነትን የክብር ፣ የመልካምነትና የእድለኝነት ተወካይ አድርገው ይወስዱታል፡፡

## 2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

የፎክሎር ጥናት መስክ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ ጥናት ተካሂዶበታል፤ እየተካሄደበትም ይገኛል፡፡ ፎክሎር የሰዎችን ማህበራዊ፣ እኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁነቶችን የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ከእያንዳንዱ የሙያ መስክ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው መስክ ነው፡፡ ከስነፅሑፍ፣ ከስነምህዳር፣ ከማህበራዊና ተፈጥሯዊ የጥናት መስኮች ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ በሚጠኑበት ንድፈ ሀሳቦች መጠናት የሚችልም መስክ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ጥናቱን ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ንድፈ ሀሳቦች ምንነትና የትኩረት አቅጣጫቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ንድፈ ሀሳብ አንድ ነገር ከምን አንፃር መታየት ወይም መጠናት እንዳለበት የሚያመላክት ወይም አንድ ነገር ማለትም አንድ የፎክሎር ቅንጣት በየትኛው የዕውቀት መስክ መጠናት

እንዳለት የሚያመላክት የጥናቱ መንገድ ቀያሽ ወይም ትልም ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የግራኝነት እምነታዊና ማህበራዊ ፍልስፍና በየትኛው የፎክሎር ንድፈ ሀሳብ እንደሚጠና ማመላከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.2.1. ፍካሬ ልቡናዊ ንድፈ ሀሳብ (Psychoanalytical theory)

ይህ የፎክሎር ንድፈ ሀሳብ በስነልቡና አስተምህሮ ውስጥ ጉልህ ስፍራ የሚሰጠውና የፍካሬ ልቡና (Psychoanalysis) መስራች የሆነው ሲግመንድ ፍሮይድ (1856-1939) አስተሳሰብን መሰረት ያደረገ ነው፡፡... ፍሮይድ ከህልም በተጨማሪ ሚቶች፣ አምልኮዎች፣ ተረቶችና ‹ሀራም› (ታቡ) የሆኑ ጉዳዮች በሰው ልጅ የኢ-ንቁው የአዕምሮው ክፍል ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተሸሽገውና ታምቀው የቆዩ ድብቅ ፍላጎቶችን የሚገልፁ መሆናቸውን በተለያዩ ስራዎቹ አሳይቷል (ሰሎሞን፣ 2007፤ 77)፡፡

ትንታኔ ስነልቡና በርካታ ስነልቦናዊ ጉዳዮች ማለትም ከአስተሳሰብና አመለካከት እንዲሁም ከስዕብና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ይበልጥ ለማጥናትና ለመተንተን አመቺ የሆነ የጥናት ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብም አጥኚው ከሚያካሂደው ጥናት ርዕስ ጋር ተቀራራቢነት ያለው Jennifer R. (2006) ‹‹ psychosocial differences between left-handed and Right handed children››. ጥናት የዚህን ንድፈ ሀሳብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም ከግራኝነት ጋር በተያያዘ ግራኝ የሆኑ ግለሰቦች ላይ የሚደርሰውን አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ እንዲሁም የማህበረሰቡ አመለካከት ለማንነት ዕድገት ግንባታ ያለውን ፋይዳ በዚህ ንድፈ ሀሳብ ለማጥናት አመቺ ነው፡፡ ቢሆንም ማህበራዊ ትዕምርትነቱንና የግራኝነት ትምዕርትነት አቀራረብ ወይም አገላለፅ ሂደቱን እንዲሁም ሎራዊ አቀራረቡን ከባህሉ ባለቤቶች ጠይቆ ለመሰብሰብ  አመቺ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡

## 2.2.2. የትዕምርታዊነት ንድፈ ሀሳብ (symbolic Theory)

ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብ የጥናት መስክ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በፈለግ ደረጃ በፎክሎር ውስጥ እየሰራ የሚገኝ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡  በአንትሮፖሎጂ የትናት መስክ ውስጥም በስፋት የሚታወቅ ነው፡፡ አንትሮፖሎጂና ፎክሎር ራሳቸውን የቻሉ የጥናት መስኮች ቢሆኑም ‹‹ፎክሎር በሚያጠናቸው ርዕሰ ጉዳዮች፣ በመረጃ አመራረጥ ዘዴዎች፣ በመረጃ አሰባሰብ

ዘዴዎች፣ በሚጠቀማቸው የጥናት ዘዴ እንንዲሁም መሰረት በሚያደርጋቸው ንድፈ ሀሳቦች ከአንትሮፖሎጂ የጥናት መስክ ጋር ከፍተኛ ትስስር አለው፡፡››

ትዕምርታዊነት ንድፈ ሀሳብን በተመለከተ ohnson (2013) ክሊ ጌርተዝን በመጥቀስ ባህል በአንድ ግለሰብ ድርጊት ብቻ የሚገለፅ ሳይሆን ማህበረሰቡ በአብሮነት ያስቀመጣቸው ውክልናዎችና የውክልናዎቹ ትዕምርትነት የማህበረሰቡን ማንነት ለመገንባት ፋይዳ አላቸው፡፡ በመሆኑም የትዕምርታዊነት ንድፈ ሀሳብ ትኩረት ትዕምርቶቹ ምን አይነት መልዕክት እንዳላቸውና እውነታዊ ገፅታው በትዕምርቱ ውስጥ የተገለፀበትን መንገድ በመተንተን ማሳየት እንደሆነ ይገልፃል፡፡

አጥኚው ለሚያካሂደው ጥናት ትዕምርታዊነት ንድፈ ሀሳብ በይበልጥ ተመራጭ የሆነ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ምክንያቱም የግራኝነት ትዕምርትነት ማለትም የካፋ ብሔረሰብ ግራኝነትን በምን አይነት መልኩ እንደሚገልፀው የሚገለፀውን እሳቤና ተወካዩን ግራ አካልን በይበልጥ ለመተንተን ትዕምርታዊነት ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ ነው፡፡

በአጠቃላይ የግራኝነት ማህበራዊና እምነታዊ ፍልስፍና ከትንታኔ ስነልቡና፣ ከትዕምርታዊ፣ ከዕድገታዊ ስነምህዳር፣ ከክሮስ ካልቸራል አንትሮፖሎጂ እንዲሁም ከትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳቦች አንፃር ሊጠና የሚችል ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ ርዕሰ ጉዳዩ ይበልጥ ትዕምርታዊነትን መተንተን ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ትዕምርታዊ የፎክሎር ጥናት ንድፈ ሀሳብንና ፍካሬ ስነልቦናን መሰረት በማድረግ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ግራኝነትን መሰረት በማድረግ በፎክሎር የጥናት መስክ የተሰሩ ጥናታዊ ፅሑፎችን ለመዳሰስ በተደረገ ጥረት በተቀዳሚነት የተዳሰሰው ጥናት Jennifer (2006) ‹‹ psychosocial differences between left-handed and Right handed children››. በተሰኘ ርዕስ የቀረበ ጥናታዊ ፅሑፍ ነው፡፡ ጥናታዊ ፅሑፉ በዋናነት ዓላማ አድርጎ የተነሳው አዎንታዊና አሉታዊ የስነልቡና ንፅፅራዊ ትንተና በግራኝ እጅ ተጠቃሚዎችና በቀኝ እጅ ተጠቃሚ ተማሪዎች ላይ ማካሄድ ሲሆን አጥኚዋ በዋናነት ሁለት የካቶሊክ ትምህርት ቤቶች በ‹‹Wichita Diocese and Reno country Kansas school›› ላይ በማተኮር በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት 132 ተማሪዎችን በመምረጥ በቃለመጠይቅ፣ በፅሑፍ መጠይቅና

በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰበውን መረጃ አይነታዊና መጠናዊ የጥናት ስልቶችን ጎን ለጎን በመጠቀም ተንትና አቅርባዋለች፡፡

በመረጃ ትንተናዋም ዓላማዋን ያማከለ ‹‹ከቀኞች ይልቅ ግራኞች ከስነልቦና አንፃር ዝቅተኛ አመለካከት (less self concept) እንዳላቸው፣ ከፍተኛ የድብርት ስሜት የሚጫጫናቸው መሆኑንና ውጫዊ ክትትል የሚያሻቸው መሆኑን›› የሚያመላክት ግኝት ላይ ደርሳለች፡፡ አጥኚዋ በዋናነት የሲግመንድ ፍሮይድስን የስነልቦና ንድፈ ሀሳብ መርሆዎች ላይ በመመርኮዝ ጥናቱን ያካሄደች በመሆኗ መርሆዎቹን በሚያመላክት መልኩ መረጃዎችን ተንትና ማቅረቧና ዓላማዋን ከግብ ማድረሷ ጥናቷ የተሳካ እንዲሆን አስችሏታል፡፡

ግራኝነትን ከባህላዊ ውክልና ወይም ትዕምርተኝነት እና ከማህበራዊ ትርጓሜ አሰጣጥ አንፃር ያልዳሰሰች በመሆኑ አጥኚው ከሚያካሄደው ጥናት ጋር እንዲላያይ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አጥኚዋ የተከተለችው ፍካሬ ስነልቡና ንድፈ ሀሳብን ሲሆን ይህ ጥናት ግን በዋናነት ትዕምርታዊነት ንድፈ ሀሳብን መሰረት የሚያደርግ በመሆኑ ሰፊ ልዩነቶችን እንዲኖሩት ያደርገዋል፡፡ ከተመሳስሎ አንፃር ግራኝነትን ለመበየንና ምን ያህሉ ግራ ምን ያህሉ ቀኝ ነው? ለሚሉ መሰረታዊ ጥያቄዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አጥኚዋ የዳሰሰችበት ሂደትና አጥኚው የሚዳስስበት መንገድ ተመሳስሎ ሊኖረው ይችላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተቃኘው ጥናት በ‹‹zakira (2022)›› ‹‹ Cultural Underpinnings on the Use of Left-Hand in Gbanjong Community of the Tolon District of Ghana›› በሚል ርዕስ የተካሄደ ጥናታዊ ፅሑፍ ነው፡፡ የጥናታዊ ፅሑፉ ዓላማ በጋና ጋባን ጆንግ ማህበረሰብ ውስጥ ግራ መሆን ያለውን ባህላዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ማሳየት ሲሆን አጥኚዎቹ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና በቡድን ተኮር ቡድን ውይይት የሰበሰቡትን መረጃ በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት በመተንተን አቅርበዋል፡፡ በዚህ መሰረትም በጋባን ጆንግ ማህበረሰብ ዘንድ ግራኝነት ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ክፍፍል እንደሌለና ከባህል አንፃር ያለው የግራና ቀኝ ክፍል ሁለንተናዊነት ያለው ማለትም ዓለም አቀፋዊ የሆነ እሳቤ ላይ የተመረኮዘ መሆኑን የሚያላክት መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡
ይህ ጥናት ግራኝነትና ቀኝነት ከባህል አንፃር እንዲሁም ከእምነት አንፃር መዳሰሱ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የጋባን ጆንግ ማህበረሰቦች ግራኝነትንና ቀኝነትን የሚያዩበትን አተያይ የዳሰሰ በመሆኑም የእኔ ጥናትም ግራኝነትን በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ያለውን

አተያይ ትንተና ለማካሄድ ትኩረት ያደረኩ እንደመሆኑ መጠን ከጥናት ቦታና ከተወሰኑ ጉዳዮች ልዩነት በስተቀር ተመሳስሎዎች አሉት፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የተዳሰሰው ጥናታዊ ፅሑፍ Alhassan (2017) ‹‹Left Handedness, The Bible and The Qur'an: Implications for Parents and Teachers›› ዋነኛ ዓላማው ግራ እና ቀኝ የአካል ክፍሎች ወይም ግራና ቀኝ እጅ በመፅሐፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁርአን ምን ያህል ጊዜና በምን አይነት መልኩ እንደቀረበ ማሳየትና ግራኝ የሆኑ ተማሪዎችን በምን አይነት መንገድ ማስተናገድ እንደሚገባ አቅጣጫ መጠቆም ሲሆን በተለያዩ ስልቶች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በገላጭ ትንተና ስልት በመተንተን አቅርቧል፡፡ በበትንተናውም ቀኝ እጅ በመፅሐፍ ቅዱስ  አንድ መቶ ጊዜ፤ ግራ ደግሞ ሃያ አምስት ጊዜ የቀረበ ሲሆን ሃያ አምስቱም አሉታዊ ይዘትን ይዘው እንደቀረቡ አመላክቷል፡፡ አያይዘውም ግራኝ የሆኑ ተማሪዎች አሉታዊ የሆነ አመለካከት በራሳቸው ላይ እንዳይኖር መምህራን ከማህበረሰቡ አመለካከት ወጣ ባለ መልኩ ግራኝነትን እንደመልካም አጋጣሚና ችግር ፈቺ እንደሆኑ አስበው እንዲያድጉ ማስተማር እንዳለባቸው አስተያየቱን ይሰጣል፡፡

ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ግራኝነትን ከእምነታዊ እይታ አንፃር ማንሳቱ ነው፡፡ ነገር ግን ጥናቱ በመፅሐፍ ቅዱ እና ቅዱስ ቁርአን ላይ እንዲሁም ተማሪዎች ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ከማህበራዊ ፍልስፍናና ባህል ጋር ያለውን አተያይ ያልዳሰሰ በመሆኑና የእኔ ጥናት እነዚህ የተጠቀሱትን ርዕሰ ጉዳዮች የሚዳስስ በመሆኑ ልዩነቶች ይኖሩታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በዳሰሳ የቀረቡ ሶስት ጥናታዊ ጽሑፎች ግራ ወይም ግራኝነት ላይ ትኩረት ያደረጉ በመሆናቸው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳስሎ አላቸው፡፡ ነገር ግን ግራኝነት ከማህበራዊና እምነታዊ ፍልስፍና አንፃር ባለመዳሰሳቸው ማለትም እንደሀገራችን ባህል ብሎም ከካፋ ማህበረሰብ ትዕምርትነት አንፃር የማይዳስሱ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ይለያሉ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

## 3.1 የጥናቱ ስልት

ጥናቱ ዓይነታዊ የአጠናን ስልትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ‹‹በምርምር ሂደት ሁሉም ነገሮች በቁጥር የሚገለጡ ወይም የሚወከሉ አይደሉም፡፡ ተመራማሪው ለማጥናት የፈለገው ጉዳይ በመጠን ሳይሆን በአይነት ይሆናል፡፡ ስለዚህ በአይነታዊ ምርምር ተመራማሪው የሚያጠናቸው ጉዳዮች በመጠን ይህን ያህል ተዛምዶ ወይም ልይይት አላቸው ብሎ ያገኛቸውን መረጃዎች በስታቲስቲካዊ ዘዴ አይገልፃቸውም፡፡ መረጃዎቹን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ለአንባቢ የሚያቀርበው ትረካዊ ወይም ገለፃዊ መንገድን ተከትሎ ነው፡፡ የመረጃ አሰባሰቡም ሆነ አተናተኑም ከመጠናዊ ምርምር ይለያል ያለው (1998፣ 20)፡፡››

እንዲሁም ይህ ዘዴ የተለያዩ የጽሁፍ መዛግብትን ለመጠቀም ከማስቻሉ በተጨማሪ ቀመራዊ ወይም ቁጥራዊ አህዝ የሌላቸውን ምርምሮችን ለማካሄድ የሚያስችል መሆኑን Best (1981:28) ያስረዳል፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ስልትን በተከተለ መልኩ ከመስክ የተሰበሰበው መረጃ በገለፃና በመፈከር ቀርበዋል፡፡

## 3.2. የመረጃ አቀባዮች ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በደቡብ ምዕራብ ክልል በካፋ ማህበረሰብ ተተኳሪነት ሲሆን በካፋ ዞን አስራ አንድ ወረዳዎችና አንድ ከተማ አስተዳደር ማለትም የዞኑ ዋና ከተማ ቦንጋ የሚገኙ ሲሆኑ በታላሚ ናሙና አመራረጥ ስልት ሁለት ወረዳዎች ማለትም ጠሎና ዴቻ ወረዳዎች እንዲሆም ቦንጋ ዙሪያ የተመረጡ የጥናት ቦታዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የጥናት ቦታዎች በዋናነት የተመረጡበት ምክንያት አስፈላጊውን መረጃ በተገቢው ሁኔታ ለማግኘትና የመረጃዎችን ትክክለኛነት ለማጣራት አመቺ በመሆናቸው እንዲሁም ግራን መሰረት ያደረጉ መረጃዎችን ከባህልና ከእምነት አንፃር መስጠት የሚችሉ መረጃ አቀባዮች ያሉባቸው በመሆኑ ነው፡፡ ሁለቱ ወረዳዎች በወስጣቸው በርካታ ቀበሌዎችን የያዙ

በመሆናቸው የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ ታላሚ የናሙና አመራረጥ ስልትን የተከተለ ነው፡፡

ለዚህ ጥናት መሳካት አስፈላጊውን መረጃ የሰጡት ከእያንዳንዱ ቀበሌ ማለትም ከአራት ቀቤለዎች ከእያንዳንዳቸው አስራ ሁለት አስራ ሁለት በድምሩ አርባ ስምንት እንዲሁም ከቦንጋ ዙሪያ ስድሰት በጠቅላላ ሃምሳ ሰባት (54) መረጃ አቀባዮች በታላሚ ናሙና ዘዴ (purposive sampling) ተመርጠዋል፡፡

> ‹‹በዚህ የንሞና ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ነው፡፡ እነማንን ብመርጥ የሚፈለገው መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ? የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ቢሳተፉ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ሰዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ይመርጣል፤ ያለው 1998፣ 132)፡፡››

በመሆኑም የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረሰ ከግራኝነት ጋር ተያይዞ በቂ መረጃ መስጠት ይችላሉ ተብለው የታሰቡ መረጃ አቀባዮች በታሚ ንሞና ዘዴ ተመርጠው በማህበረሰቡ ዘንድ የግራኝነት እሳቤ ወይም ግራኝነት እንዴት እንደሚገለፅ መረጃ አቀብለዋል፡፡

ከታላሚ የንሞና ዘዴ በተጨማሪ ጠቋሚ የንሞና ዘዴ በጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ጠቋሚ የንሞና ዘዴን አስመልክቶ ያለው እንዳወቅ እንዲህ ይገልፃሉ፡፡

> ጠቋሚ ንሞና (Network or snowball sampling) አንዳንድ ጊዜ ተመሪማሪው ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ያሏቸውን ሰዎች በቅርብቢኖሩም እንኳ ለይቶ ለማግኘት አስቸጋሪ የሚሆንበት ወቅት አለ፡፡ እነዚህ ሰዎች በጥናቴ አካላይ ውስጥ ተበትነው በትክክል የት እንዳሉ ለማመልከትና ካለበት ሄዶ ለማግኜት አዳጋች ይሆናል። በዚህ ወቅት ተመራማሪው ጠቋሚ ንሞናን እንዲጠቀም ሁኔታዎች ያስገድዱታል። በጠቋሚ ንሞና ተመራማሪው በሚያጠናው ችግር ዙሪያ እውቀቱ ያለው አንድ ሰው ወይም ቡድን ያገኝና የተወሰነ መረጃ ይሰበስባል፡፡ ሲጨርስ እንደሱ በሚያጠ ናው ችግር ዙሪያ ተመሳሳይ መረጃ ሊሰጡት የሚችሉ ሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች ካሉ እንዲጠቁመው ይጠይቃል:: በጥቆማው መሠረት ቀጣዮቹን ያገኝና መረጃውን ይሰበስባል:: እንደጨረሰም ሌሎችን እንዲጠቁሙት

ይጠይቃል፡፡ እንዲህ እያደረገ የሚፈልገውን መረጃ ለማግኘት ከአንዱ ጠቋሚ ወደሌላው ተጠቋሚ ሂደቱን ይቀጥላል፡፡ ያለው (2009፣ 134)

ስለግራኝነት ማህበራዊ አመለካከት መረጃ እንዲሰጡ በታላሚ የንሞና ዘዴ ከተመረጡ መረጃ አቀባዮች በተደረገ ጥቆማ መሰረት ከጠሎ ወረዳ አራት፣ ከቦንጋ ዙሪያ ስድስት በድምሩ አስር መረጃ አቀባዮች በጠቋሚ የንሞና ዘዴ ተመርጠው የተለያዩ መረጃዎችን ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ በታላሚና በጠቋሚ የንሞና ዘዴ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተመሳሳይነት ወይም ተቀራራቢነት ያላቸው በመሆኑ የንሞናው ቁጥሩ በስልሳ ሰባት (64) መረጃ አቀባዮች ላይ ቁጥሩ እንዲገደብ አድርጓል፡፡ ይህም ሲባል ታላሚ የንሞና ዘዴ ከተመረጡ መረጃ አቀባዮች በጠቋሚነት የተመረጡ መረጃ አቀባዮች የተሰበሰበው መረጃ ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከስልሳ አራቱ መረጃ አቀባዮች መካከል ሃያው (20) ቁልፍ መረጃ አቀባይ በመሆን ተመርጠዋል፡፡ ከእነዚህ መረጃ አቀባዮች መረጃዎችን ለመሰብሰብም የአንድ ወር ያህል ጊዜ ፈጅቷል፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህንን ጥናትና ምርምር ለማካሄድ በዋናነት ተግባር ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፡- ሰነድ ፍተሻና ቃለመጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.3.1 ቃለመጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ ፈቃደ (2001፡90) እና ሌሎችም ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ አውዳዊ ጥናት ለሚያካሂድ ተመራማሪ የሚያገለግል መሆኑን እና በዋናነት መረጃው የሚሰበሰበው በሶስት ዘዴዎች እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ዘዴዎቹም ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታና ተተኳሪ የቡድን ውይይት ናቸው፡፡

ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ከዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል ቃለ መጠይቅ አንዱ ነው፡፡ በመሰረቱ ቃለ መጠይቅ በቃል የሚቀርብ መጠይቅ ነዉ፡፡ በጠያቂዉና በተጠያቂዉ መካከል የፊት ለፊት የቃላት ምልልስ ያለበት ነዉ፡፡ ይህ

የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚፈለገውን መረጃ ለማግኘት የሚያስችል፣ ለመረጃ አቀባዩም ነጻነት የሚሰጥ እና በመረጃ አቀባዩ እና በመረጃ ሰብሳቢው መካከል መልካም የሚባል ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችል ዘዴ እንደሆነ Goldstein (1964፡108) ያስረዳሉ፡፡

እንደ ፊቃደ (1991፣101-2) አገላለጽ ሁለት አይነት የቃለ መጠይቅ የጥያቄ አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም ክፍት ጥያቄዎችና ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ ዝግ ሲባል ቁርጥ ያለ መልስ ለማግኘት፣ እንቅጯዊ መረጃ ለማግኘት የሚጠየቁ ጥያቄዎች ናቸዉ፡፡ ክፍት ጥያቄዎች የሚባሉት ‹ጥያቄው የሚቀርብለት ሰዉ ብዙም ሳይጨነቅ ነፃ (flexible) ሆኖ፣ አንዳንድ ወነችን እያመጣ፣ የራሱንና የሌሎችን ሰዎች ስሜትና አስተያየት እየጠቀሰ የሚመልሳቸዉ ጥያቄዎች ናቸዉ፡፡

በዚህ መሰረትም ስለግራኝነት ማህበራዊ አመለካከት ከተመረጡት ናሙናዎች ዝግ የሆኑ ቃለ መጠይቆችን በመጠቀም አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ስነቃል ውስጥ እንዳለና እንደሌለ፣ ግራኝነት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት እንዳለውና እንደሌለው ለመሳሰሉት አጭር መልስ ለሚሹ ጉዳዮች ዝግ ቃለመጠይቅ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ከግራኝነት ጋር ተያይዞ የገጠማቸውን ስነልቦናዊና ማህበራዊ ጫናዎችን በተመለከተ፣ ግራኝነት በብሔረሰቡ ዘንድ ምን አይነት ትዕምርትነት እንዳለው፣ ግራኝነትን መሰረት ያደረጉ ክልከላዎች ከምን እንደመነጩ፣ ከቤተሰብ አንፃር ግራኝነት እንዴት እንደሚታይና ከእነዚህና መሰል ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ላላቸው መልስ ለሚሹ ጉዳዮች ክፍት ቃለ መጠይቅ ተግባር ላይ ውሏል፡፡

## 3.3.2 ሰነድ ፍተሻ

ሰነድ ዳሰሳ ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና ስልቶች አንዱ ነው፡፡ ሰነድ ዳሰሳ ማለት ከጥናቱ ርዕሰ-ጉዳይ ጋር ተዛማጅ የሆኑና መረጃ ሊሰጡ የሚችሉተን የተላያዩ መፃሕፍት፣ መጣጥፎችን፣ የግልና የድርጅት ማህደራትን፣ ብሮሸሮችን...ወዘተ. ፍተሻ ማድረግ ነው፡፡ የሰነድ ዳሰሳ ሊሰራ ከታሰበበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጥናቱ ፍፃሜ ድረስ የሚከናወንና በእያንዳንዱ የጥናት ስራና የጥናት ክፍሎች ውስጥ ከትልመ ጥናት ዝግጅት አንስቶ እስከ መረጃ ትንተና ድረስ ባሉት ተግባራት ሁሉ የሚከወን የጥናትና ምርምር ሂደትና ተግባር ነው፤ ያዴሳ (2006፣108)፡፡

በመሆኑም ከግራኝነት ጋር ተያይዞ በብሔረሰቡ ዘንድ የተነሱ ማህበራዊም ሆነ እምነታዊ እሳቤዎች በተለያዩ መፃሕፍት፣ መፅሔት፣ ጋዜጦች፣ ብሮሸሮችና በመሳሰሉት ተፅፈው ከታተሙ የመረጃ ምንጮች አስፈላጊው መረጃ በሰነድ ፍተሻ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ ሰነድ ፍተሻ ካዕላይ የመረጃ ምንጭ እንደመሆኑ መጠን ወደመስክ ከመከሄዱ በፊት አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግና መሰረታዊ የምርምር ጥያቄዎችን ወደአካባቢያዊ ጥያቄዎች ማለትም ለመረጃ አቀባዮች ግልፅ በሆነ መንገድ ለማዘጋጀት ትልቁን ሚና ተጫውቷል፡፡

> "እኔ እስከማውቀው ድረስ ማንኛውም መስከኛ በተለይ ለስራ ወደ ገጠር የሚሰማራ… በባዶ ሆድ መስክ አይወጣም፡፡ የስነቃል ተመራማሪውም…ለመስክ ስራ በባዶ ሆድ ለመስክ ስራ መውጣትን አያስብም፡፡ የሚሆን ነገር አይደለም፡፡ በዚህ ዓይነት በባዶ ራሱ መስክ መሰማራት የለበትም፡፡ እዚያ ሔጄ ምን እንደምጠይቅና ምን እንደምሰራ አስባለሁ ማለት አይፈቀድለትም"ፌቃደ (1991፡124-125)

ይህንን መነሻ በማድረግም ግራኝነት በካፋ ማህበረሰብ ስነቃል ውስጥ ምን አይነት ትዕምርትነት እንዳለው ከታተሙ መፃሕፍት፣ መፅሔቶችና የተለያዩ ፅሑፎች በሰነድ ፍተሻ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ከፅሑፎች በተገኘው መረጃ ለቃለመጠይቅ ጥያቄዎች መነሻ ግብዓት በመሆን አግልግሏል፡፡

## 3.4. የመረጃ መቅረጫ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት ዓላማ ከግብ መድረስ በዋናነት ማስታወሻ ደብተር፣ መቅረፀ ድምፅና መቅረፀ ምስዕል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት የመረጃ መወቅረጫ መሳሪያዎች የራሳቸው የሆነ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚናዎች አሏቸው፡፡ በመሆኑም መቅረፀ ድምፅ በመጠቀም መረጃ መስጠት ፍቃደኛ ካልሆኑ ተጠኚዎች መማስታወሻ ደብተር አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡

በመቅረፀ ድምፅ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ከሆኑ መረጃ አቀባዮች መቅረፀ ድምፅን በመጠቀም ጎን ለጎን ማስታወሻ በመያዝ መረጃውን መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ሁለቱን በአንድነት መጠቀሙ መረጃዎችን እያመሳከሩ ለመተንተን ጉልህ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

## 3.5. የመረጃ አደረጃጀት

አንድ ተመራማሪ ትክክለኛና አስተማማኝ የመረጃ መሰብሰቢያ ተጠቅሞ ተገቢ የሆነ መረጃ መሰብሰቡ የምርምር አንዱና ዋናው አካል ቢሆንም የጥናቱ መጨረሻ ደረጃ ላይ ደርሷል አያስብለውም፡፡ ከመረጃ ስብሰባ በኋላ አግባብ ያለው የትንተና ዘዴ መጠቀም ቀጣዩ ሂደት ነው፡፡ የተጠቀመበት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለሚደርስበት የውሳኔ ሀሳብም ሆነ የጥናቱ ማጠቃለያ ወሳኝነት አለው፡፡ ትንተናውን ለማካሄድ እንዲቻል መረጃው ለትንተና በሚያመች መልክ ተደራጅቶ ተቀናጅቶና ትርጉም በሚሰጥ መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ይህን የማድረግ ሂደት ነው ቅድመ የመረጃ ትንተና የሚባለው፡፡ መረጃ ተሰበሰበ ማለት ወዲያውኑ ለትንተና ተዘጋጀ ወይም ትንተና ይካሄዳል ማለት አይደለም፤ (ያለው፤1998፤233)፡፡

አንድ ተመራማሪ የተለያዩ የመረጃ መሰበሰሰቢያ ዘዴዎችንና መሳሪያዎችን ተጠቅሞ መረጃዎችን ከሰበሰበ በኋላ ቀጣዩ ስራው ሊሆን የሚችለው የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመልክ በመልኩ ማደራጀት ነው፡፡ መረጃዎችን ሰበሰበ ማለት በቀጥታ ወደ ትንተናውና የመፍሄ ሀሳቦች ይገባል ማለት አይደለም፡፡ ይልቅ ለስራው ቅልጥፍናና የተደበላለቁ ሀሳቦችን ለመለየት በስርአት ተደራጅተውና ፈር ይዘው መሰናዳት አለባቸው፡፡ ያለበለዚያ መውረጃ እንደሌለው ጎርፍ መሄጃ መንገዱ ይጠፋብናል፡፡ በመሆኑም አጥኚው የጥናቱን ዓላማ መሠረት ባደረገ መልኩ ከመስክ በቃለ መጠይቅ፤ እንዲሁም ከሰነድ ፍተሻ ያሰባሰባቸውን መረጃዎች የተለያዩ ኮዶችን በመስጠት፣ የሚቀነሱትን መረጃዎች በመቀነስ፣ መረጃዎችን በማጣራትና በማመሳከር ለመረጃ ትንተና አመቺ በሆነ መልኩ አደራጅቷል፡፡

## 3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ይህ ጥናት በዋናነት የግራኝነት ማህበራዊና እምነታዊ ፍልስፍና ትንተና ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ አይነታዊ የጥናት ስልትን የተከተለ ነው፡፡ ስለዚህ ገላጭ የመረጃ ትንተና ዘዴን በዋናነት ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ገለጭ የትንተና ስልትን በሚከተልበት ወቅትም ትዕምርታዊ ጉዳዮችን ገላጭ የሆነ ትርጓሜና ፍከራ በመስጠት የተሰበሰበውና የተደራጀው መረጃ በምዕራፍ አራት ስር ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

## 3.7. የጥናቱ ስነምግባራዊ ጉዳዮች

ጥናትና ምርምር የራሱ የሆነ ቅደም ተከተልና አደረጃጀት እንዲሁም የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ደረጃዎች ያሉት ሂደት በመሆኑ አጥኚው ሊከተላቸው የሚገቡ መርሆችና ስነምግባራዊ ጉዳዮች አሉ፡፡

> the goal of human research often include understanding real-life phenomena, studying effective treatments, investigating behaviours, and improving lives in other ways. What you decide to research and how you conduct that research key ethical considerations. This considerations works to protect the rights of research participants, enhance research validity and maintain scientific or academic integrity. (scribbr.com. **May 9, 2024.**)

የምርምር ተቀዳሚው ዓላማ እውነተኛውን ህይወት መረዳት፣ ትክክለኛውን ሂደትና ስነባህሪ መከተል እና ችግሮችን ለመቅረፍ ሌላ ስልት መፈለግ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይህንን ተግባር ለማከናወን የምርምር ስነምግባራዊ ጉዳዮችን ከግምት ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡ ተገቢ የሆኑ ተጠኚዎችን የመምረጥ፣ የጥናቱን ትክክለያነትና ብቁነት ለማረጋገጥ የምርምር ሙያዊ ስነምግባር አስፈላጊ እንደሆነ ፅሑፉ ያስረዳል፡፡

በመሆኑም የጥናት የስነምግባር ደንቦችን መከተል ከላይ የተጠቀሱትን ጠቀሜታዎች ወይም ትኩረት ቢደረግባቸው የሚኖራቸውን አስተዋፅኦ መነሻ በማድረግ በመስክ መረጃ አሰባሰብ ወቅት አጥኚው የመረጃ አቀባዮችን ስሜት፣ ፍላጎትና ምስጢር በመጠበቅ፣ ባህላቸውን፣ እሴቶቻቸውንና የአመጋገብ ስርዓታቸውን በመከተል፣ አስፈላጊውን የመረጃ መቅረጫ የመምረጥና በመጠቀም እንዲሁም ከግል ስሜት ነፃ የሆኑ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ ለጥናት መስክ በወጣበትም ወቅት አጥኚው ከሚማርበት የትምህርት ክፍል ማንነቱንና የጥናቱን ርዕስ የሚገልፅ ደብዳቤ በመያዝ ለተጠኚዎች በመስጠትና የጥናቱን ዓላማና ጠቀሜታ በመግለፅ ተገቢውን የመተማመን ስሜት በመፍጠር መረጃዎችን ሰብቧል፡፡

የተሰበሰበውን መረጃ በመተንተን ሂደትም ከመስክ የተሰበሰበው መረጃ ትክክለኛ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ ለመተንተን ጥረት አድርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት


## የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ

### 4.1. መልካዓ ምድራዊ ዳራ

የካፋ ዞን ዋና ከተማ ቦንጋ ሲሆን ከአዲስ አበባ 499.7 ኪሎሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ እ.አ.አ በ2007 በተደረገው የህዝብ ቆጠራ 858,600 ያህል የህዝብ ብዛት እንደነበራት መረጃው ያመላክታል፡፡ በቀድሞ የአስተዳደር ስርዓት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ክልላዊ መንግስት ስር ዞን ስትሆን በአሁኑ ወቅት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ክላስተር ዋና መቀመጫ ከተማ ናት፡፡ በካፋ ዞን አስራ ሁለት ወረዳዎችና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች ይገኛሉ፡፡ አብዛኛው ህዝብ ካፌቾ ሲሆን  ከኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 12% ያህሉን የሚዝ ሲሆን ሌሎች በርካታ ብሔሮችችም በዞኑ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህል ዳውሮ (በከፋ ምስራቃዊ አካባቢዎች መካከል ራሳቸውን ያቋቋሙ)፣ የናኦ ብሔረሰብ (በደቡብ ካፋ የሚኖሩ ናቸው)፣ ጫራ (በሰሜን የሚኖሩ በኦሞ ወንዝ፣ በምስራቅ ካፋ) እና ሚኤኒቲ (በደቡብ ካፋ የሚኖሩ) በአብነት ይጠቀሳሉ። የካፋ ብሔረሰብ ቋንቋ ካፊ ኖኖ ሲሆን በዞኑና በወረዳዎች የስራ ቋንቋ በመሆን እያገለገለ ይገኛል፡፡

ዞኑ ከአንፃራዊ መገኛ ቦታ ገለፃ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ከኦሮሚያ ክልል ጋር ድንበርተኛ ነው። በምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ከኮንታ ልዩ ወረዳ ጋር፤ በደቡብ ከደቡብ ኦሞ ዞን ጋር ድንበር ይጋራል። በደቡብ ምዕራብ ክፍል ደግሞ በቤንች ማጂ ዞን ጋር ይዋሰናል፡፡ በካርታ ላይ ደግሞ ከፋ ዞን በደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍል በ60 24’ እስከ 7 06° 24’ to 7° 70’ ውስጥ ይገኛል። ሰሜን እና 35° 69’ እስከ 36° 78’ ምስራቅ፣ ከአዲስ አበባ ደቡብ ምዕራብ 460 ኪ.ሜ ርቀት ላይ። ከፋ ዞን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መንግስት የሚገኝ ሲሆን ከ6° 24’- 8° 13’ ሰሜን ኬክሮስ እና 35° 30’ - 36° 46′ ምስራቅ ኬንትሮስ ውስጥ ይገኛል። የዞኑ አጠቃላይ ስፋት 10.636 Skm2 ሲሆን ይህም ከክልሉ አጠቃላይ ስፋት 7 በመቶውን ይይዛል። (ገሊላ፣ 2021፣ 22)




የካፋ ዞን ካርታ

በካፋ ዞን የሚገኙ ጎሳዎች የሚያሳይ ካርታ

## 4.2. የካፋ ጥንት አመጣጥ ታሪክ

የሀገራችን ጥንታዊ ታሪክ በአብዛኛው የተጠናው በሀገር ውስጥ አጥኚዎች ሳይሆን በውጭ ሀገር ዘጎች ነው፡፡ የካፋ ብሔረሰብ ጥንት አመጣጥ ታሪክም በስፋት የተጠናው በውጭ አጥኚዎች እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የካፋ ብሔረሰብ ከየት መጣ ለሚለው ጥያቄ በቀለ (1996፣70-75) እነላንጌንና ሌሎች የውጭ ታሪክ አጥኚዎችን በመጥቀስ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

> ከአባይ ወንዝ በስተሰሜንና በአብዛኛው በስተደቡብ እስከ ስምጥ ሸለቆ ባለው ሰፊ ሀገር የጎንጋ ሕዝቦች ሰፍረውበት እንደነበር ብዙ የታሪክ ፀሀፊዎች ገልፀዋል:: ጎንጋ ሕዝቦች የሚባሉት በዋናነት የዛሬዎቹን የካፋ፣ የሸካ፣ የሂናሮ፣ የአንፊሎ ወይም ቡሻሼ፣ የሺናሻ (የቦሮ)፣ እንዲሁም የቦሾ ወይም የጋሮ ህዝቦችን ያካትታል፡፡ እነዚህ ህዝቦች የታሪክ የባህልና የቋንቋ ቅርበትና ትስስር እንዳላቸው ከላይ በተዘረዘሩትና በሌሎችም ፀሐፊዎች ተረጋግጧል፡፡ የጎንጋ ሕዝቦች በአብዛኛው ምንጫቸው ከግብፅና ከየመን ሆኖ በኋላም የአባይን ሸለቆ በመከተል ጎንደር፣ ጎጃምና፣ ትግራይ አካባቢ እንደኖሩና ቀጥለውም ወደ ደቡብ እንደፈለሱ ይነገራል:: በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ ጦርነቶችና በተለይም የኦሮሞ መስፋፋትና ግፊት ለእነዚህ ህዝቦች መበታተንና መክሰም ምክንያት ሆኗል ተብሎ

ይታመናል። በመሆኑም የቦሮ ሺናሻ ሕዝብ ከአባይ በስተሰሜን በዛሬው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን ይገኛል፡፡ የቦሻ ወይም ጋሮ ህዝብ ደግሞ ከጎጀብ በስተምሥራቅና ሰሜን በጎጀብና በግቤ ወንዞች መገናኛ አካባቢ፣ በአሁኑ የኦሮሚያ ክልል ከጅማ ምሥራቅና ምሥራቃዊ ሰሜን አካባቢ ይገኛል:: የቦሻና የአንፌሎ ህዝቦች በተለይ ከሺናሻ ጋር ቅርበት ያላቸው ሲሆን በአሁኑ ጊዜም በኦሮሞ በመዋጣቸው ከጥቂት የዕድሜ ባለፀጎች በስተቀር በአብዛኛው የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው:: የአንፈሎ (ቡሳሴ ወይም ቡሻሼ) ሕዝብ በአሁኑ የኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የእነዚህም ባህልና ቋንቋ በአሁኑ ጊዜ በኦሮሞ ተውጧል፡፡

የሂናሮ (እናሪያ) መንግሥት ሥሙጥርና ሃይለኛ ሆኖ እስከ 16ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ግዛቱን በምሥራቅ በኩል እስከ ጊቤ ወንዝ ድረስ አስፋፍቶ ሲኖር ከኦሮሞ ጋር ባደረገው ያላቋረጠ የሃያ ዓመታት (1558-1578) ጦርነት ድል ሆኖ ሕልውናውን አጥቷል:: በሌላ በኩል ክሪሚ የተባለ ፀሐፊ የእናሪያ መንግሥት ጨርሶ የወደመው በ1710 እንደሆነ ገልፆ፣ ‹ከዚህም የተነሣ የገኘሮው መደብና ሕዝቡ በባህልና በደም ወደሚቀርበው ካፋ ተሰዱል› ይላል፡፡ የቀሩትም በአሁኑ የጅማ ዞን እንደሌሎቹ በኦሮሞ ተውጠው የሚገኙ ሲሆን፣ አብዛኛው የሂናሮ ዝሪያ ግን ዛሬ በሰሜን ምሥራቅ ካፋ ከጎጀብ ወንዝ በስተምዕራብ ይገኛል፡፡ ዝርያቸውም አሁንም ሂናሮ ተብሎ ሲጠራ፣ የሌሎች አብረውት የተሰደዱ ጎሳዎች መጠሪያ መነሻ ሆሂያቸውም በ"ሂን" ይጀምራል፡፡ ለምሳሌ ሂንማቾ፣ ሂንጉኖ፣ ሂንባሮ፣ ሂንገቾ እና ወዘተ የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

ከላይ የቀረበው የታሪክ መረጃ የካፋ ህዝብ ከጎንጋ ህዝቦች ስር የሚመዘዝና ዋነኛ ምንጩ ግብፅና የመን እንደሆነ እንዲሁም የጎንጋ ህዝቦችን አንድነትና ክፍፍል፣ የአሰፋፈር ሁኔታዎችን ያሳያል፡፡ የጎንጋ ህዝቦችም የራሳቸውን ስርወ መንግስት በመመስረት ‹‹ከአባይ በስተደቡብና በምዕራብ አቅጣጫ እስከታላቁ ስምጥ ሸለቆና ሩዶልፍ ሐይቅ ድረስ ይዘልቅ›› እንደነበረ የቢቤርና ግሩል (1920 እና 1932) ፅሑፎች ያመላክታሉ፡፡

## 4.3. ጥንታዊ ነገስታትና የአስተዳደር ስርዓት

ካፋ ከ13ኛዉ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እጅግ ጠንካራና የተደራጀ መንግስትና ንጉሳዊ አገዛዝ ስርዓት ያለዉ እጅግ የሰለጠነና የተደራጀ የፖለቲካ መዋቅር እንደነበረዉ ሰፊ የታሪክ ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዋናነት የሶስት ዝርያ ወይም ጎሳ አባላት እነርሱም የመንጃ፣ የማቶና የሚንጆ ስርወ መንግስታት መፈራረቃቸውን፤ የማቶ ነገስታት ከ14ኛው ክ/መ

በፊት ጀምሮ የካፋ ገገሮች የነበሩ ሲሆን በ14ኛው ክ/መ ስልጣኑን ለሚንጆ የገገር መደብ ማስረከቡን በቀለ (1996፣ 75) ገልፀዋል፡፡

ሰስለካፋ ወይም ስለጎንጋ ህዝቦች ታሪክ በስፋት ካጠኑት አጥኚዎች መካከል አንዱ ላንጌ ነው፡፡ ላንጌ (1982፣197) በካፋ ስርወመንግስት የተፈራረቁ ነገስታትንና የንግስናቸውን ዘመን እንደሚከተለው አስፍሮታል፡፡

| ተ/ቁ | የነገስታት ስም | የንግስና ዘመን | | ተ/ቁ | የነገስታት ስም | የንግስና ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምንጂሎቺ | 1390-1425 | | 11 | ጋሊ ጋዮቺ | 1742-1765 |
| 2 | ሾንጌ ታቶ | 1425-1460 | | 12 | ሻጊ ሻሮቺ | 1765-1768 |
| 3 | አዲዬ ታቶ | 1460-1495 | | 13 | አቤቲ ሂኖቺ | 1768-1776 |
| 4 | ሻዴ ታቶ | 1495-1550 | | 14 | በሺ ጊኖቺ | 1776-1798 |
| 5 | ማዲ ጋሮ | 1550-1565 | | 15 | ሆቲ ጊኖቺ | 1798-1821 |
| 6 | ቦንጌ ታቶ | 1565-1605 | | 16 | ጋኼ ነቾቺ | 1821-1841 |
| 7 | ጊቤነቾቺ | 1605-1640 | | 17 | ካዊ ኤሮቺ | 1841-1843 |
| 8 | ጋሊ ጋሮቺ | 1640-1675 | | 18 | ካጂ ሼሮቺ | 1843- 1868 |
| 9 | ጋሊ ጊኖቺ | 1675-1710 | | 19 | ጋሊ ሼሮቺ | 1868-1890 |
| 10 | ጋሊ ጋዮቺ | 1710-1742 | | 20 | ጋኪ ሻሮቺ | 1890-1897 |

ይን ጥንታዊ መንግስት በበላይነት በንጉሱ ወይም በንጉሰ ነገስቱ የሚመራ ቢሆንም ‹‹ምክረቾ›› አማካሪ ካብኔ የነበረዉ ሲሆን አመራረጡም በችሎታና በስነምግባር ላይ የተመሰረተ እንደሆንነ መጽሐፍት ይገልጻሉ፡፡ ንጉሱ የበላይ መሪ ቢሆንም ጉዳዮችን የመፈጸም ትልቁ ስልጣን የ‹‹ጉጂ ራሾ›› ነዉ፡፡ በአሁኑ ወቅት ጠቅላይ ሚንስተር እንደማለት ነዉ፡፡

በካፋ የአዉራጃ ገገሮች ‹‹ወራፌ ራሾ›› ወይም ‹‹ወራቤ ራሾ›› የሚባሉ ሲሆን አዉራጃዎቹ ደግሞ ‹‹ወራፌ ሾዎ›› እንደሚባሉ ላንጌ (1982፣215) ይገልጻል፡፡በካፋ ንግስና ስርዓት ዉስጥ የሚኒስተሮች ሹመት ደረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህም›፡-

- ካተሜ ራሾ፡ ⟶ የመከላከያ ሚኒስተር
- አዋ ራሾ ፡ ⟶ የፍትህ ሚኒስተር
- አዲዮ ራሾ፡ ⟶ የግንባታ (ኮንስትራክሽን)ሚኒስተር

➢ ቦዲ ራሾ፡ ⟶ የንጉስ አማካሪ
➢ ሾዴ ራሾ፡ ⟶ የማህበራዊ ደህንነት ሚኒስተር
➢ አርቹ ራሾ፡ ⟶ የኮሚኒኬሽን ሚኒስተር (ምንጭ ቦሮ ትዩብ ሰኔ 27/ 2018)

በአጠቃላይ የካፋ ብሔረሰብ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር በአብሮነትና በመፈቃቀር የሚኖር ብሔረሰብ ሲሆን ጥንታዊ የሆነ የአስተዳደር ስርዓት ያለው፣ በጥብቅ ደኑ የሚታወቅ፣ ቡናን ለዓለም ህዝብ ያስተዋወቀና ስነምህዳራዊ ገፅታውን መንግስታዊ ባልሆነ ‹‹ናቡ›› በተባለ ድርጅት የሚያስጠብቅና የሚያስጠና አካባቢ ነው፡፡ በፎክሎርና በአንትሮፖሎጂ እንዲሁም በሌሎች የጥናት መስኮች ሊጠኑ የሚችሉ በርካታ ባህላዊ ዕሴቶች ባለቤትም ጭምር ነው፡፡

## 4.4. የካፋ ብሔረሰብ ባህላዊ ዕምነቶች

የካፋ ብሔረሰብ የክርስትናና እስልምና እንዲሁም ሌሎች እምነቶች ከመስፋፋታቸው አስቀድሞ የራሱ የሆነ ሀገረሰባዊ ዕምነት ያለው ብሔረሰብ ነው፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ ሀገራባዊ ዕምነቱ ‹‹Eqqo›› (ኤቆ) የሚል ሲሆን እምነቱን የሚያራምዱ ወይም የእምነቱ መሪዎች ‹‹አላማሞ›› ወይም በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ኤቄ ናዬኖ›› በመባል ይታወቃሉ፡፡ የእምነቱ መሪ የሆኑ ‹‹አላሞዎች›› በአማርኛ አቻ ትርጉም ቃልቻዎች በአካባቢው ለሚገኙ ማህረሰቦች በህመም ወቅት መድሃኒት የሚቆርጡ፣ ወደፊት ምን ሊከሰት እንደሚችል የሚተነብዩና በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን Gellila (2021) ገልፃለች፡፡

ብሔረሰቡ በወረዳ የተዋቀረ እንደመሆኑ መጠን ወረዳዎች ላይ ያለው የዕምነቱና የመሪዎች ስያሜ የተለያየ ነው፡፡ ለአብነት ያህል ‹‹ Damochechi›› (ዳሞቼቺ) በጨና አካባቢ፣ ‹‹Yaferochi› (ያፌሮቺ) እና ‹‹ Wogidochi›› (ወጊዶቺ) በአዲዮና ሽራዳ አካባቢ›› እውቅና እንዳላቸው መጥቀስ ይቻላል፡፡ በአዋናነት ግን ‹‹ኤቆ›› የሁሉም ማዕከላዊ እምነት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ከሀገረሰባዊ እምነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ‹‹ዴጆ ነው፡፡ ‹‹ካፋ ውስጥ አዲስ ሰብል በተለይም በቆሎና ጤፍ ሲደርስ ከመቀመሱ በፊት በባህሉ መሠረት ከሰብሉ የተሰራ የምግብና የመጠጥ ናሙና ከእንስሳት መስዋዕት ጋር ይቀርባል፡፡ ይህም ሂደት ዴጆ (Deejjo) ወይም ቆሌ ዴጆ (Qoollee Deejjoo) ይባላል:: ደጆ በሚደረግበት ወቅት ዶሮ፣

በግ፣ ፍየል፣ ወይም በርካታ ሰዎች የተሳተፉበት ከሆነና አቅም ከፈቀደ ደግሞ ያልተቀጠቀጠ በሬ ወይም ኮርማ ታርዶ ከዓይነቱ ከተጠበሰ በኋላ ከአዲሱ እህል በፈሳሽነትና በምግብነት ከተዘጋጀው እህል ጋር ይቀርባል፡፡ የሚቀርበውም ምግብ የበሰለና ሽታ ያለው መሆን እንዳለበትና የዴጆ ዋና ዓላማ በአካባቢው ጥጋብና ሠላም እንዲነግሥ ብሎም ረሀብና በሽታ እንዲርቅ፣ እና ለተገኘው ምርት አምላኩን ለማመሥገን እንደሆነ በቀለ (1996፣ 60) እና ሰለሞን (2013፣ 24-28) ገልፀዋሉ፡፡

## 4.5. የአየር ንብረት ሁኔታና ምርቶች

በካፋ ብሔረሰብ ዞንድ ሶስት ወቅቶች አሉ፡፡ ‹‹Angesho›› ደጋ፣ ‹‹Guddifoo›› ወይናደጋ እና ‹‹Worefo›› ቆላ በማለት የሚመደቡ ናቸው፡፡ አብዛኛው የዞኑ አካባቢዎች በደጋ የአየር ንብረት ክልል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የደጋው አየር ንብረት በጣም ቀዝቃዛ በመሆኑ ለከብትና በግ እርባታ፣ ለንብ እርባታና የተለያዩ አዝዕርቶችን እንደባቄላ፣ ስንዴ፣ ገብስና የመሳሰሉትን እንዲሁም በአካባቢው ሰፊ ስፋት ያለውን የእንሰት ተክል ለማምረት ተመራጭ ነው፡፡ ወይናደጋው አየር ንብረት በሁለተኛ ደረጃ በስፋት ህዝቦች ሰፍረውበት የሚገኘው የአየር ንብረት አይነት ሲሆን በዚህ አየር ንብረት ባለበት አካባቢ በቆሎ፣ ግብሰ፣ ጤፍና የመሳሰሉ አዝዕርቶች በስፋት ይመረታሉ፡፡ ቆላ የአየር ንብረት በጣም ሞቃታማ የአየር ንብረት ሲሆን በአካባቢውም ማሽላ፣ በቆሎና ጤፍ በስፋት እንደሚመረት የ(MOA, 2000) መረጃ ያሳያል፡፡

የካፋ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ የዝናብ መጠን የሚያገኝ አካባቢ እንደሆነ እንደቦንጋ የአየር ትንቢያ ጥንቅር ባለሙያዎች ገለፃ መሰረት የካፋ ማዕከላዊ አካባቢዎች በዓመት ከ1300 እስከ 2000mm እንደሚያገኙ ገልፀዋል፡፡ ይህም ለጥቅጥቅ ደን መፈጠርና ቀጥሎ በቀረበው መረጃ ውስጥ የተጠቀሰው የ‹‹ቆሌ ዴጆ›› ስርዓት አምልኮ መኖር ትልቁን ድርሻ ይወስዳል ማለት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## የመረጃ ትንተና

የካፋ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የአምልኮ፣ የአስተዳደር፣ የአኗኗርና የአለባበስ እንዲሁም የማንነቱ መገላጫ የሆኑ ትውፊቶች ባለቤት የሆነ ብሔረሰብ ነው፡፡ ብሔረሰቡ በባህሉም ሆነ በዕምነቱ ውስጥ ባህላዊ እሳቤዎችን የሚያንፀባርቁ የተለያዩ ክንዋኔዎችን ያከናውናል፡፡

የካፋ ብሄረሰብ እንደሌሎች ብሄረሰቦች ሁሉ ቀደምት ባህላዊ እምነቶች ወይም ሀገረሰባዊ ዕምነቶች አሉት፡፡ በካፋ ያሉ ጎሳዎች (gumbo) (ጉምቦ) የየራሳቸዉ አምልኳዊ መናፍስት አሏቸዉ፡፡ እነዚህም መናፍስት ‹‹eqqo›› (ኤቆ) የሚባሉ ሲሆን እነዚህን መናፍስት የሚመሩ መንፈሳዊ መሪዎች ‹‹aalamoo›› (አላሞ) በመባል ይታወቃሉ፡፡

በእነዚህ እምነቶች ስርዓት ከበራ ወቅት የሚከወኑ የተለያዩ ተግባራት የብሔረሰቡን እሴትና ባህል በጠበቀ መልኩ ይፈፅማሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ብሔረሰቡ ዕምነት መሰረት ለ‹‹ኤቆ›› መስዕዋት በሚቀርብበት ወቅት የሚቀርበው መስዕዋት በሬ ከሆነ ከቀለም አንፃር ጥቁር አለመሆኑ፣ ከዕሳቤ አንፃር ሻኛው ወደ ግራ ያለመውደቁ፣ ዶሮ ከሆነ ኳንኩ ወይም ኮከኑ ነጠላና ድምድም፣ ነጠላ ከሆነ ወደግራ ወይም ወደ ቀኝ መውደቁ ትኩረት ተደርጎበት ይመረመራል ወይም ይመረጣል፡፡ ማንኛውም እንስሳ ለእርድ ስለደረሰ ብቻ ለመስዕዋትነት አይቀርብም፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ ግራኝነትን መሰረት አድርገው የቀረቡ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 5.1. ግራኝነት ከፍትህ አሰጣጥና ከጦረኝነት አንፃር ያለው ትዕምርትነት

ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ከተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች አንፃር የተለያዩ ምልከታዎች ወይም ማህበራዊ ትርጉሞች አሉት፡፡ ከእነዚህም መካከል በፍትህ ዘርፍ ወይም በዳኝነት ስርዓት ውስጥ ግራኝነት ቀና ያልሆነ ወይም የተንጋደደ ተደርጎ የሚወሰድበት አጋጣሚ እንዳለ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የጥናቱ መረጃ አቀባዮች የባህል ሙዚቃ ተጫዋች አቶ አባተ እና የካፋ ብሔረሰብ ታሪክ አዋቂና ዳኛ አቶ አሰፋ ከዳኝነት ስርዓት ጋር ተያይዞ ግራኝነት ምን አይነት ትርጉም እንዳለው እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

በባህላዊ ፍርድ አሰጣጥ ሂደት የከሳሽና ተከሻሽ አቋቋም፣ ከዳኛው ፍርድ አሰጣጥ እስከ ክርክሩ ረችና ተረች ያለውን ሂደት ስናይ ለግራ የተሰጠው ትርጉም አሉታዊ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሰዎች በባህሉ መሰረት ወደ ሽማግሌ ሂደው የሚያመለክቱት በደል ስለደረሰባቸው ፍትህ እንዲሰጣቸው ነው፡፡ ተበዳይ ካለ በዳይ ይኖራል፡፡ ፍርዱ ምንም ይሁን በዳይነት በበጎ አይታይም፡፡ በዳይ ተብሎ የሚታሰበው ተከሳሽ በግራ እንዲቆም መደረጉ ከዚሁ ባህላዊ እምነት የሚመነጭ ነው፡፡ ባህላዊ ዳኛ የግራ ቀኝ ጉዳዩን አይቶ ትክክለኛ ፍርድ እንዲሰጥ ይጠበቃል፡፡ ፍርድ ማዛባት፣ ፍትህን ማጓደል ከግራ ጋር ተያይዟል፡፡ ከክርክሩ በኋላ እውነትን ይዞ ከረታ በግራ የነበረ ተከሳሽ በቀኝ ሲቆም፣ በቀኝ የነበረ ከሳሽ በግራ ይቆማል፡፡ በዚህ የፍርድ ሂደት  ቀኝ የእውነተኛነትና ሚዛናዊነት  ግራ ደግሞ የአጥፊነትና የፍርደ ገምድልነት ትርጎም ይዘው መግባታቸውን መረጃው ያሳያል፡፡

ግራኝነት እንደዚህ አይነት ማህበራዊ ትርጉም ስለሚሰጠው ግራኝ የሆኑ ሰዎች ከተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎዎች ይከለከሉ እንደነበርና አልመው የማይስቱ ቢሆንም ክልላው እንደሚያግዳቸው የሚከተለው መረጃ ያሳያል፡፡

> በካፋ ብሔረሰብ ውስጥ በንጉሱ ዘመን ወይም በንጉሳዊ አስተተዳደር ዘመን ግራኝ የሆነ ሰው ለወታደርነት ለ‹‹ኢራሾ›› አይመረጥም፡፡ እኔ እሰከማውቀው እስከ አ1960ዎቹ ድረስ ግራኝ የሆነ ሰው አይጨበጥም ወይም የእጅ ሰላምታ አይሰጠውም፡፡ በሹመትና ፍርድ አሰጣጥ ሂደቶች ላይም ተሳታፊ አይሆንም፡፡ ‹እሱ ግራ ሆኖ፣ ግራኝ የሰይጣን ሆኖ እንዴት የተቃና ፍርድ ሊሰጥ ይችላል?› በማለት ማህበረሰቡ ለሹመት አያጨውም፡፡ የወለደ አባትም ‹ወንድ አልወለድኩም፣› ሴት ስትሆንም ለነገስታትና ለጦር ሹማምንት ሚስትነት መታጨት ስለማትችል ‹ባሪያ ሆና ትኑር›  በማለት ሀዘኔታቸውን ይገልፃሉ (ጉጄ ራሻ አሰፋ፣ የካቲት 5/2016)፡፡

በአጠቃላይ ከፍትህ ስርዓት አንፃር ፍትህን አንፃር ግራኝ የኢፍትሃዊነት ትርጓሜን ይዞ ቀርቧል፡፡ በስልጣን እርከን ውስጥም የኢፍትሃዊነት ትርጓሜ የተሰጠው በመሆኑ ግራኝ የሆኑ ሰዎች ከስልጣንና አዎንታዊ ጠቀሜታ ካለቸው ማበራዊ መስተጋብሮች የሚገለሉበት ሂደት እንዳለ መረጃው ያሳያል፡፡

## 5.2.ግራኝነት በጋብቻ ስርዓት ውስጥ ያለው ትዕምርትነት

በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ጋብቻ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ማህበራዊ ሁነት ነው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ዘንድ ሶስት አበይት ነጥቦች ጋብቻ እንዳይካሄድ ሊያግዱ ይችላሉ፣ እነዚህም ‹‹ ተመሳሳይ ዘር ጎሳ መሆን፣ በማህበራዊ ህይወት የተፈጠረ ዝምድና እና የዘር ሀረግ ግንድ ተመሳስሎ›› እንደሆነ አቶ ማርቆስ (2002) ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ጥናት ትስስር ያለው ሁለተኛው ነጥብ ነው፡፡ በማህበራዊ ህይወት ኪፈጠሩ ዝምድናዎች መካከል አንዱ በጋብቻው ወቅት ከወንዱ ሚዜዎች ጋር የሚፈጠር ዝምድና ነው፡፡ አቶ ማርቆስ (2002) የዚህን ዝምድና ትስስርም እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> የካፋ ብሔረሰብ ለዝምድና ትልቅ ቦታ ይሰጣል፡፡ ዝምድናዉንም በተለያየ መንገድ ይመሰርታል፡፡ በክርስትና አባትነት ወይም እናትነት፣ በአይን አባትነት ወይም እናትነት፣ እንዲሁም በጋብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ በጋብቻ ወቅትም የተለየ ዝምድና ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይሄዉም የሚዜነት ዝምድና ነዉ፡፡ በአከባቢዉ ባህልና ልማድ መሰረት ሚዜ ለወንዱ ብቻ ነዉ የሚያስፈልገዉ፡፡ ሴቷ ወደ ወንዱ ቤት ስትሄድ የወንድዬዉ እናት ወይም እህት ናቸዉ እንክብካቤ የሚያደርጉላት እንጂ ሚዜ የላትም፡፡ የወንዱም ቢሆን (yoochee miyaato) የግራ ሚዜ ና (qaane miyaato) የቀኝ ሚዜ የሆኑ ሁለቱ ብቻ ናቸዉ፡፡ ይህን የሚዜነት ምርጫ ጎሳን መሰረት ያደረገ ሲሆን ሚዜዎቹ ከተጋቢዉ ቤተሰብ ጋር ዝምድና ስለመሰረቱ በምንም አይነት መንገድ ከነሱ ጋር ጋብቻ መፈፀም አይችሉም፡፡

በቀድሞ ስርዓት በብሔረሰቡ ዘንድ ሴት ልጅ ግራ መሆን ወይም ማንኛውንም ተግባር በግራ መፈፀም ለጋብቻ ተመራጭ ላያደርጋት እንደሚችል አባቶች ይናገራሉ፡፡
ለጋብቻ በሚደረግ ሂደት ማለትም በመረጣና በመተጫጨት ወቅት የግራኝነት ወይም ግራ የመሆንና አለመሆን መስፈርት ከወንዱ ይልቅ በሴቷ ላይ የበለጠ የጠበቀ እንደነበር የካፋ ባህል ሙዚቃ አቀንቃኝና ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋች የሆኑት አቶ አባተ አቤቶ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> *በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ሴት ልጅ ግራኝ ከሆነች ለትዳር ማንም ወንድ አይፈልጋትም ወይም ተመራጭ አትሆንም፡፡ በመሆኑም እናቶች ሴት ልጆቻቸው ግራኝ እንዳይሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ፡፡ በግራ እንዳትጋግር፣ በግራዋ ቆሎ*

*እንዳትቆርጥ፣ በግራዋ ቡና እንዳትቀዳ፣ በግራ ቤት እንዳትጠርግና ማንኛውንም ተግባራት በግራ እንዳታከናውን እየተከታተለች ክልከላ ታደርጋለች፡፡*

*ግራኝ የሆነች ሴት በትዳር ወቅት ተመራጭ የማትሆንበት ዋነኛ ምክንያት በረከት የላትም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ በግራዋ ጋግራ ምታበላው ምግብ አያጠግብም ወይም ግራ ስለሆነች በረከት ቤት ውስጥ አይኖርም፡፡ ግራ የሰይጣን ተደርጎ ስለሚታሰብ የበረከት መንፈስ ወይም መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን እርኩስ መንፈስ ወይም ሰይጣን በግራዋ ላይ ስለሚያድር በረከት ረድኤት አይኖርም ተብሎ በማህበረሰቡ ዘንድ ስለሚታሰብ ነው (የካቲት 6/ 2016)፡፡*

ከዚህ መረጃ የግራኝነት አፍራሽ ማህበራዊ ክልከላ በሴቶች ላይ እንደሚያይልና ስርዓተ ፆታዊ አንደምታ እንዳለው ያሳያል፡፡ ግራኝነነት ከሰይጣንና ከበረከተ ቢስነት ጋር እንደሚገናኝም ተገልጿል፡፡

ሌላው በብሔረሰቡ ዘንድ ከጋብቻ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የግራኝነት አሉታ ከሚዜ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በአብዛኛው የከተማው ማህበረሰብ ዘንድ ሙሽሮች በወንዱ ወገንና በሴቷ ወገን ሚዜ ይኖራቸዋል፡፡ ሚዘዎቹም አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶሰስተኛ ከፍ ሲልም አራተኛ እየተባለ ደረጃ ይሰጣቸዋል፡፡ በካፋ ብሔረሰብ በባህላዊ ጋብቻ ወቅት ሚዜ የሚያስፈልገው ለወንዱ ብቻ ሲሆን የወንዱ ወገን ሚዜዎቹም የቀኝ ሚዜ ‹‹qaanee miyaatoo›› (ቃኔ ሚያቶ) እና የግራ ሚዜ ‹‹yoochee miyaatoo›› (ዮቼ ሚያቶ) በመባል ይሰየማሉ፡፡

የቀኝ ሚዜ ‹‹qaanee miyaatoo›› (ቃኔ ሚያቶ) በጋብቻ ሂደት ውስጥ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወት ግለሰብ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶም መረጃ አቀባዮች አቶ አሰፋ፣ አቶ ቦጋለ፣ አቶ አጦ ወዶ(የካቲት 6/2016) የሰጡት ምላሽ ወይም ገለፃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*በባህላዊ ጋብቻ ወቅት የሴት ሚዜ ሚባል ነገር የለም፡፡ ሚዜ ለወንድ ብቻ ነው፡፡ ወንዱ የግራና የቀኝ ሚዜዎች ይኖሩታል፡፡ የግራና የቀኝ ሚዜ ልዩነት የቀኝ ሚዜ ማለት የሙሽራው ወሳኝ የሆነ፣ የሚታመንለት፣ ገመና ከታቹና በጋብቻው ወቅት ማንኛውንም ተግባር የሚከውን የልብ ወዳጅ ነው፡፡ ቀኝ ሚዜ ከአግቢው ጋር ጥብቅ ትስስርን ለመመስረት የሚመረጥ ነው፡፡ በካፋ ባህል የካፋ ብሔረሰብ ለዝምድና ትልቅ ቦታ ይሰጣል፡፡ ዝምድናዉንም በተለያየ መንገድ ይመሰርታል፡፡ በክርስትና*

አባትነት ወይም እናትነት፣ በግርዛት ጊዜ በአይን አባትነት ወይም እናትነት፣ እንዲሁም በጋብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ በጋብቻ ወቅትም የተለየ ዝምድና ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይሄዉም የሚዜነት ዝምድና ነው፡፡ ሚዜዎቹ ከተጋቢዉ ቤተሰብ ጋር ዝምድና ስለመሰረቱ በምንም አይነት መንገድ ከነሱ ጋር ጋብቻ መፈፀም አይችሉም፡፡ የጋብቻ ክልከላው በይበልጥ በቀኙ ሚዜ ላይ የፀና ይሆናል፡፡ ታማኝነትም ኖሮት ነው የሚመረጠው፡፡ ሙሽራዋ እስክትላመድ ድረስ ከሙሽራው ቤት አስገዳጅ ካልሆነ ከአራት ቀን በፊት ከሙሽሮቹ ቤት አይወጣም፣ ከወጣም እየተመላለሰ የመንከባከብ ግዴታም አለበት፡፡ በመሆኑም የቀኝ ሚዜ ትልቅ ተአማኒነት ያለው ችግሮችን መጋፈጥ የሚችልና ለዝምድና ትልቅ ቦታ ያለው ነው፡፡ ሙሽሪት ዐይነአፋር ወይም ልብስ ለማውለቅ ፈቃደኛ ባትሆን አስፈላጊውን ትብብር የሚያደርገው የቀኝ ሚዜ ነው፡፡ ተአማኒነቱ እስከዚህ ድረስ ነው፡፡

የግራ ሚዜ በተለየያዩ ምክንያቶች መነሻነት ይመረጣል እንጂ እንደቀኝ ሚዜ ጉልህ ሚና ይኖረዋል ተብሎ አይደለም፡፡ አንደኛው ምክንያት ዝምድና ለመፍጠር ሲባል ሁለተኛ በብሔረሰቡ ዘንድ ከሚመነጭ አፈታሪክ መሰል ነገር ማለትም ‹በሙሽራው ግራ በኩል ሰይጣን አለ፣ በመሆኑም ሙሽራውን ሰይጣን እንደይለክፈው ግራ ሚዜ ያስፈልጋል፡፡› የሚል አመለካከት በመኖሩ ምክንያት የግራ ሚዜ ይመረጣል፡፡ እንዲሁም የቀኝ ሚዜ ረዳት ወይም አጋዥ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብም ጭምር የግራ ሚዜን ይመረጣል፡፡ ሚናው የቀኝ ሚዜ ያህል ባለመሆኑ ‹‹ቢቸግር ወይም ባጣቆይ›› የሆነ ነው፡፡ ተአማኒነቱ ያነሰ ነው፡፡ የቀኝን ያህል አይደለም፡፡

በቀረበው መረጃ መሰረት በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ቀኝ ሚዜ ከግራ ሚዜ ይበልጥ ተአማኒነት ያለውና ከሙሽራው ጋር ለወደፊቱም ጥብቅ ዝምድናን በመፍጠር እንደዘመድ በመቆጠር ከሙሽራ ዘር ሀረግ ጋር ጋብቻን መመስረት እስከመከልከል ደረጃ የሚደርስ ሲሆን ግራ ሚዜ ብዙም ተአማኒነት የሌለው፣ ዝምድና እንደመፍጠሪያ አማራጭና ለቀኝ ሚዜ ረዳት ተብሎ የሚመረጥ ብቻ ሳይሆን ሙሽራውን በስተግራ በኩል ሊያሰናክል ከሚችል እርኩስ መንፈስ እንዲከላከል ታስቦ የሚመረጥ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

ሌላው ከጋብቻ ጋር ተያይዞ ሙሽሪት በሰርጉ ዕለትም ሆነ ከሰርጉ በኋላ ከሙሽራው በሰተቀኝ በኩል እንድንትቀመጥና እንድትተኛ አይፈቀድላትም፡፡ ዘወትር መተኛት ያለባት

በስተግራ በኩል መሆን እንዳለበት የካፋ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆኑ ሽማግሌዎች ይገልፃሉ፡፡ ይህ አመለካከት እምነታዊና ማህበራዊ የግራኝነት እሳቤ ላይ መሰረት ያደረገ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሔዋን ከአዳም ግራ ጎን ከመገኘት ጋር ወይም የህጥያ ምንጭ ከመሆኗ ጋር ሊያያዝ ይችላል፡፡ በበባህሉ ሴት በወንድ ፍቃድ የምታድር ታዛዥ በመሆኗ ይንንም ላማሳየትም ሊሆን ይችላል፡፡

## 5.3. የግራ ትርጉም በእንስሳት አካላት አፈጣጠር ላይ

ግራን መሰረት በማድረግ ወይም ወደግራ ያዘነበሉ የሰውነት ክፍሎችን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ባህላዊ ትርጉሞችን መስጠት በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ የተለመደ ተግባር ነው፡፡

በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ሻኛው ወደ ግራ የወደቀ ወይም ያዘነበለ በሬ ለእርድ ተመራጭ አይሆንም፡፡ በይብልጥ ደግሞ ለአምልኮ ስርዓት ማለትም ለመስዕዋትነት ፈፅሞ አይቀርብም፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ለእርሻም ቢሆን አይመረጥም፡፡ ለመስዕዋትነት የማይቀርብበት ዋነኛ ምክንያት ለአምላክ ወይም ለአድባር መልካም የሆነውን ነገር ለመስጠት ከመሻት አንፃር በመሆኑ ግራ የሆነ ነገር የክፋት ተምሳሌት ነው ብለው ስለሚታመን ነው፡፡ ለእርሻ የማይመረጥበትም ምክንያት ‹እርሶ አያጠግብም፣ በረከት የለውም› ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ሻኛው ወደግራ የወደቀ ወይም ላዘነበለ በሬ አጣማጅ ወይም በብሔረሰቡ አጠራር ‹qaro› ማግኘት ከባድ ስለሆነ በገበያ ውስጥም ተፈላጊ አይደለም፡፡

ሻኛው ወደግራ ያዘነበለ በሬ አርሶ ጎተራ አይሞላም፣ በቤት ውስጥ ከብት አያኖርም ተብሎ በብሔረሰቡ ዘንድ ይታሰባል፡፡

ለገጠሩ ማህበረሰብ ፈረስ ዘርፈ ብዙ ጥቅም አለው፡፡ ከእነዚህም መካከል የመጓጓዣ አገልግሎቱ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው፡፡ በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ አንዱ የጀግንነት ወይም የወንድነት መገለጫ ደህና ጋላቢና ፈጣን የኮርቻ ፈረስ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ በመሆኑም ጥሩ ፈረስ ጋላቢዎች ፈረስ በሚገዙበት ወቅት የጋማውን አወዳደቅ ወዴየት እንደተኛ ወደቀኝ ወይም ወደግራ መሆኑን እንዲሁም ከእግሮቹ ከናች ከፍ ብሎ የሚፈጠር ነጭ ክብ ቀለበት መሳይ መስመር ‹qoobeeboo› (ቆቤቦ) በቀኝ ወይም በግራ እግሩ ላይ መሆኑን በውል ይመለከታሉ፡፡ ጥሩ ጋላቢ፣ ለኮርቻ ምቹና ባለቤቱን የማይጥል ምርጥ ፈረስ ተብሎ ሊመረጥ የሚችለው ጋማው ወደቀኝ

> ያዘነበለና ነጭ ክብ ቀለበት መሳይ መስመር በቀኝ እግሩ ላይ ያለው ፈረስ ነው፡፡ (አጦ ገብሬ፣ የካቲት 8/ 2016)

በብሔረሰቡ ዘንድ ጋማው ወደግራ ያዘነበለ ፈረስ ለግልቢያ አይሆንም፣ ቢሆንም ባለቤቱን ይጥላል የሚል ዕምነት በመኖሩ ምክንያት ተመራጭ አይሆንም፡፡

> አውራ ዶሮ ኳንኩ ወይም ኮከኑና የጭራው ላባ ወደ ግራ ያንጋደደ ከሆነ ወይም ወደ ግራ ካዘነበለ ለማንኛውም ሐይማኖታዊ ተግባር አይሰዋም፡፡ በብሔረሰቡ እምነት ወይም አባባል እንዲህ አይነት አውራ ዶሮ ‹‹maashiqaarete›› (ማሽቃረቴ) ይባላል፡፡ በመሆኑም ለአምልኮ ስርዓት በምንም አይነት መልኩ እንደዚህ አይነት ዶሮ አይቀርብም፡፡ የመስዕዋት ስርዓቱን ለቀጣይ ያሽጋግራል እንጂ በፍፁም አያርድም፡፡ ምክንያቱም ለአምላኩ ማለትም ዶቺ፣ ጨዮ፣ አሼሎቺ፣ ቆሎ፣ እና የመሳሰሉት መስዕዋት ለሚቀርብላቸው መናፍስት መጥፎን መርጦ እንደመስጠት ይቆጠራል፡፡ (አቶ አሰፋ ገ/ማሪያም የካቲት 8/ 2016)

ከዚህ በላይ ከበሬ፣ ከፈረስና አውራ ዶሮ ጋር ተያይዘው የቀረቡ የእንስሳት አካል ወደ ግራ ሲወድቅ የሚሰጠው ባህላዊ ትርጉም በረከት አልባ ከመሆን፣ የክፋት ተምሳሌት ከመሆን፣ አስቸጋሪ ወይም የመጥፎ ነገር ተምሳሌት ከመሆን ጋር የተያያዘ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ብሔረሰቡ ጥቁርና አካላቸው ወደግራ ያዘነበሉ እንስሳትን ተፈጥሮና ድረጊታቸውን ከሰይጣንነት ጋር ያያይዘዋል፡፡ ለምሳሌ ‹‹አንዲት ላም የበረቱን ግራ እንጨት ወይም ምሰሶ ዘወትር ማታ ማታ የምትልስ ከሆነ፣ የከብት በረከት ታሳጣለች ተብሎ ወዲያውኑ ትሸጣለች፡፡›› ይህም በብሔረሰቡ ዕሳቤ መሰረት ግራኝነት በእንስሳት ላይም ከአሉታዊነት ጋር የተያያዘ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## 5.4. የግራኝነት እሳቤ በብሐረሰቡ ስነቃል ውስጥ

### 5.4.1.ግራኝነትና ሚት

በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ በስፋት የሚታወቅ ግራኝነትን መሰረት ያደረገ አንድ አፈታሪክ እንዳለ መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ፡፡ የብሔረሰቡ ተወላጆችም ግራኝነትን ከሰይጣን ጋር

እንዲያያይዙ ዋነኛ መነሻ የሆናቸው ጉዳይ እንደሆነም ያምናሉ፡፡ በመሆኑም ግራኝነት ከሰይጣን ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑንን የሚያመላክተውን አፈታሪክ የካፋ ባህልና ታሪክ አዋቂ አቶ አሰፋ(የካቲት 9/ 2016 እና 22/ 2016) የሚከተለውን መረጃ ሰጥተዋል፡፡

> በድሮ ጊዜ ውሃ ልክ እንደሚዳ ለጥ ብሎ የተኛ ሀይቅ ነበር አሉ፡፡ ከዚያን ሰይጣንን የፈጣሪን ሃያልነት ለመፈታተንና ሁሉንም ነገር እራሱ ሰይጣን ማድረግ እንደሚችል ለማሳየት ሲል ወደእግዚአብሔር ዘንድ ቀረበና ‹ይህን ባህር አድርገህ የሰራኸውን የተኛ ውሃ እጄን በማንሳት አንድ መስመር ይዞ እንዲፈስና እንዲሄድ ማድረግ እችላለሁ› ሲል ተናገረ፡፡ እግዚአብሔርም ‹እሲቲ አድርገዋ› ሲል ምላሽ ሰጠ፡፡ ሰይጣንም ሆን ብሎ ለማሳሳት ያቀደ በመሆኑ ‹የትኛውን እጄን ላንሳ? ግራዬን ወይስ ቀኜን?› ሲል እግዚአብሔርን ጠየቀ፡፡ እግዚአብሔርም ‹ቀኙማ የእኔ ነው ግራህን አንሳ› ብሎ መለሰለት፡፡ ሰይጣንም ግራ እጁን አንስቶ እንደባህርና ሀይቅ የተኛውን ውሃ ሲያዘው አንድ መስመር እየያዘ እንደጅረት መፍሰስ ጀመረ፡፡ እግዚአብሔርም ‹ከአሁን በኋላ የጅረት ወይም የወንዝ ጥጋጥጎች የአንተ መስፈሪያ (መኖሪያ) ይሁኑ ሲል ረገመው፡፡ ለዚህ ነው በወንዞች አካባቢ ሰይጣን ይኖራል የሚባለው፡፡

‹‹ግራ የሆነ ነገር ሁሉ የሰይጣን ነው፡፡›› የሚል አመለካከት በብሔረሰቡ ዘንድ ስር የሰደደ አመለካከት እንደሆነ ቀደም ሲል በተነሱት መረጃዎችታይቷል፡፡ ከላይ የቀረበው ሚት በብሔረሰቡ ዘንድ ትልቅ አመኔታዊ ተቀባይነት አለው፡፡ በመሆኑም ትውልዱ ይህንን ሚት በታሪክነት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በእውነትነት ተቀብሎ ይተገብረዋል፡፡ ለዚህም ማሳያው ሰይጣን በወንዞች ዳርቻ ይኖራል ተብሎ መታመኑ ነው፡፡ ወደወንዝ መሄጃ ሰዓትንም ይወስናሉ፡፡ በተለይ ከከቀኑ ስድስት ሰዓት እስከ አስር ሰዓት ባላው ጊዜ መካከል በወንዝ ዳርቻ መገኘት ለልክፍት ያጋልጣል፤ ያ ሰዓት የሰይጣን ሰዓት ነው እየተባለ የሚታመነውና ከሚቱ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የግራኝነት አሉታዊ እሳቤ በብሔረሰቡ ሚት ብቻ ሳሆን በተረቶቹም ውስጥ እንዳለ በሚከተለው ክፍል ቀርቧል፡፡

### 5.4.2.ግራኝ በተብሔረሰቡ ተረት ውስጥ

ማርቆስ (2002) ‹‹የካፋ ስነቃል›› በሚል ባሳተመው መፅሐፍ ውስጥ የተለያዩ ተረቶችን በተለያየ ርዕስ ከፋፍሎ አቅርቧል፡፡ ከእነዚህም ተረቶች መካከል ግራ ወይም ግራኝነት የተጠቀሰበት ተረት ‹‹gaanech kenaa mecho›› (ባለፀጋ ባልና ሚስቶች) በሚል እንደሚከተለው ከካፊ ኖኖ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡ በቃለመጥይቅ ወቅትም ‹‹ግምቤራሻ›› መለሰ (የካቲት 7/ 2016) ቀጥሎ የቀረበው ተረት በብሔረሰቡ ዘንድ ቅቡልነት እንዳለውም አረጋግጠዋል፡፡

> በድሮ ጊዜ ሁለት በእድሜያቸው የገፉ ባልና ሚስት አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ እነኚህ ባልና ሚስት ብቻቸውን የሚኖሩ ሲሆኑ ባለጠጎችም ነበሩ፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ባል የኮርቻ ፈረሳቸውን ጭነው ወደገበያ ይሄዳሉ፡፡ ጥቂት እንደተጓዙም አንድ ብልጥ የሆነን ሌባ አግኝተው ሰላም ብለውት ያልፋሉ፡፡ ብልጡ ሌባም የሰውየውን አለመኖር ወይም ገበያ መሄድ መሰረት አድርጎ ወደሰውዬው ሚስት ዘንድ ሄዶ ሰላምታ ከሰጠ በኋላ ከባለቤታቸው ጋር ቀጠሮ እንደነበራቸውና ዕቃ እንደሚያስቀምጡለት መነጋገራቸውንና አጋጣሚ ሆኖ ወደገበያ እየሄዱ መንገድ ላይ እንዳገኛቸው ለሴትየዋ ይነግራታል፡፡ ሴትየዋም ‹ታዲያ አሁን ምን ልርዳህ? ብላ ትጠይቀዋለች፡፡ ወደዚህ ስመጣ መልዕክት ልከውኛል፡፡ ‹በስላቻ ውስጥ አድርጌ ጓዳ ያስቀመጥኩትን ዕቃ ስጪው ብለውኛል› ሲል ይናገራታል፡፡ ሴትየዋም በአመኔታ ስልቻውን አውጥታ ትሰጠዋለች፡፡
>
> ሌባውም ስልቻውን ይዞ ከአካባቢው ትንሽ እንደተጓዘ ሰውዬው ለገበያ የሚሆን ገንዘብ ስልቻ ውስጥ ረስተው እንደመጡ ትዝ ይላቸውና ወደቤት ይመለሳሉ፡፡ ወደቤት እንደደረሱ ባለቤታቸውን ጠርተው ጓዳ ያለውን ስልቻ እንድታመጣላቸው ያዛሉ፡፡ ባለቤታቸውም ‹ተነጋግረህ ለላክከው ሰውዬ እኮ ስልቻውን ሰጥቼው አሁን እኮ ነው በዚህ መንገድ ይዞት የሄደው› ብለው ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ሰውዬውም ስልቻውን መንገድ ላይ ያገኙት ሌባ አታሎ እንደወሰደው በመገንዘብ ባለቤታቸው በጠቆመቻቸው መንገድ ሽምጥ መጋለብ ጀመሩ፡፡
>
> የስልቻው ባለቤት እየተከታተለው መሆኑን ያወቀው ብልጡ ሌባ ወዲያውኑ ስልቻወን በመደበቅ ሜዳ ላይ ወዳሉ ከብቶች በመጠጋት ከብት እረኛ መስሎ ቁጭ

ይላል፡፡ የስልቻው ባለቤት ከብት ወደሚጠብቀው እረኛ ጠጋ ብለው፣ ‹አንድ ስልቻ የያዘ ሰው በዚህ በኩል ሲያልፍ አይተሃል?› ሲሉ ይጠይቁታል፡፡ እረኛ መስሎ የተቀመጠው ብልጡ ሌባ ‹አዎን ጋሼ፡፡ አሁን በዚህ **በስተግራ** በኩል እጥፍ ብሎ ሂዷል፤ ብዙም አልራቀም ደርሰውበታል፡፡ ባይሆን ፈረሱን እዚህ እኔ ዘንድ አድርገው ይሂዱ፤ እስኪመለሱ ድረስ ከከብቶቹ ጋር እጠብቀዋለሁ፡፡› ይላቸዋል፡፡ ሞኙ የስልቻ ባለቤትም ‹እሺ ቶሎ ሌባውን ይዤ እመለሳለሁ፤ እዚሁ ጠብቀኝ፡፡› ብለው ፈረሳቸውን አስረው ብልጡ ሌባ በጠቆማቸው አቅጣጫ **በስተግራ** በኩል በእግር መሄድ ይጀምራሉ፡፡ ብልጡ ሌባም ሰውዬው ከእይታው እስኪሰወሩ ድረስ ከጠበቀ በኋላ ኮርቻ ፈረሱን እየጋለበ **በስተቀኝ** በኩል ተፈተለከ፡፡

ሞኙ ሰውዬ ከአድካሚ ጉዞ በኋላ ወደ እረኛው ሲመለሱ እረኛውም ፈረሳቸውም በቦታው አልነበረም፡፡ በጣም እያዘኑ ወደቤታቸው ተመለሱ፡፡ ወደቤት ሲመለሱም ባለቤታቸው ‹ፈረሱን የት ጥለህ መጣህ?› ብለው ሲጠይቋቸው፣ ‹አንቺ በሞኝነትሽ ስልቻውን አስወሰድሽ እኔም በሞኝነቴ ኮርቻ ፈሬሰን አስበላሁ፤ ሁለታችንም እኩል ነን፡፡› አሉ ይባላል፤ (ማርቆስ፣ 2002፣ 53-4)፡፡

ከላይ በቀረበው ተረት ውስጥ ግራ ተያይ ውስብስብ፣ አደናጋሪ፣ የማይገኝ ስውር ደባን የሚያመላክት ትርጉም እንዳለው መረጃው ያሳያል፡፡ በዚህ ተረትም ግራ ከሰይጣንነት ጋር የተያያዘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሰይጣን አታላይና አሰሳች ነው፡፡ የሚያከናውናቸው መጥፎ ነገሮች ለተታለዮቹ ግልፅ አይደሉም፡፡ ሌባው ሰውዬውን በስተግራ በኩል ሄዷል ብሎ የተሳሳተ አቅጣጫ የጠቆመው በተሳሳተ መንገድ እየዳከረ እንዲውል ለማመመላከት ነው፡፡ የብሔረሰቡ ተወላጅ  ግልፅ ያልሆነ ነገር ሌላ ሰው ሲናገር ሲሰማ ‹ንግግርህን ግራ አታድርግ ግልፅ አድርገህ ተናገር› በማለት ግራ የተወሳሰበና አደናጋሪ መሆኑን ያመላክታል፡፡ በአጠቃላይ በተረቱ ግራ ወደ እውነትነት ሳይሆን ወደ ተሳሳተ መንገድ መሄጃና ማታለያ ተደርጎ ቀርቧል፡፡

የግራኝነት እሳቤ በብሔረሰቡ ምሳሌያዊ ንግግሮች ውስጥ እንዴት እንደተገለፀ ደግሞ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 5.4.3. የግራኝነት እሳቤ በብሔረሰቡ ምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ

የካፋ ብሔረሰብ የተለያዩ እሴቶቹንና ልማዶቹን የሚገልፁ ምሳሌያዊ ንግግሮች ባለቤት ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ (1.7) ላይ በመስክ ተሞክሮ ውስጥ እንደ ችግር ለመግለፅ እንደተሞከረው በተተኳሪነት ከተመረጡ መረጃ አቀባዮች ከአንድ በላይ እንዲሁም በአጋጣሚ ከተጠየቁ ግለሰቦች ግራኝነትን መሰረት ያደረጉ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ማስታወስ አለመቻላቸው የተፈለገውን ያህል ግራኝነትን መሰረት ያደረጉ ምሳሌያዊ ንግግሮችን መሰብሰብ አልተቻለም፡፡ በተደረገው ሰነድ ፍተሻ ግራኝነትን መሰረት ያደረገ አንድ ምሳሌያዊ ንግግር ማግኘት ተችሏል፡፡ በድምሩ ግራኝነትን መሰረት ያደረጉ ሁለት ምሳሌያዊ ንግግሮች የተገኙ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. ‹‹qanno ta beetaa yoocho mii'ehe ቀኙ እኔ እያለሁ ግራው ተሸከመ፣
   Qadoo ta beetaa keepho ttatehe iye wenne›› ሰርዶ እኔ እያለሁ ሙጃው ነገሰ፡፡
   (ቦጋለና ወርቁ፣ 2006፣ 18)

ከላይ የቀረበው ምሳሌያዊ ንግግር ተጠቂነትን ወይም በወዳጅ መከዳትን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህም ቀኝና ሰርዶ ጠንካራ፣ ስር የሚሰዱ፣ ታማኝ፣ ጥብቅ የሆኑ የሚል ተምሳሌትነትን የያዙ ሲሆን ግራ እና ሙጃ ደግሞ አቅመ ቢስ፣ ተአማኒነት የሌላቸው፣ የማያዛልቁና የልፍስፍስነት ትርጉም ይዘው የቀረቡ ናቸው፡፡ እንደፅንሰ ሀሳብ በአማርኛው ‹‹ጊዜ ያነሳው ቅል ድንጋይን ይሰብራል›› ወይም ‹‹ምንቸቶች አለቁና ጋኖች ምንቸት ሆኑ›› የሚሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በአቻነት የሚተካ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፡፡ ልዩነቱ ግራኝነት በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር አቅመ ቢስና ተአማኒነት የሌለው ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ይህም ቀደም ሲል ለግራ ሚዜ ተአማኒነት እንደሚጎድለው ከተገለፀው ሀሳብ ጋር አብሮ እንደሚሄድ ለመረዳት ይቻላል፡፡

‹yoochee bakee qooxoch tach beeroo yagiiti qaana yagibebo iyee

በግራ ዶሮ ቆጥ በኩል ማደሪያ ላነጠፈችልኝ በቀኝ በኩል አንጥፊ በሏት፣

Yooxee shaatee goochochi bitoo tegiiti xoofoo mayii beeboye ta anami bushoo anaameto tane iyee wene›› (አቶ አንጋሞ የካቲት 6/2016)

በሰባራ ገል ጠጅ የቀዳችልኝን ዋንጫ እጠቢ በሏት እኔ የወንዱ ልጅ ወንድ ሆኛለሁ፡፡

በሁለተኛ ላይ የቀረበው ምሳሌያዊ አነጋገር የሚነገርበትን አውድና የመልዕክቱን ምንነት ምሳሌያዊ ንግግሩን ያቀበሉ መረጃ አቀባይ አቶ አንጋሞ እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

…ምሳሌያዊ አነጋገሩ የሚነገረው ከወንድ ልጅ ግርዛት በኋላ ነው፡፡ ድሮ ወንድ ልጆች እንደ አሁኑ በሰባት፣ በዘጠኝ ወይም በአስር ቀን ሳይሆን የሚገረዙት ከሰባት አመት በላይ ሲሆኑና ነፍስ ሲያውቁ ነበር፡፡ በዚያ ወቅት ማደንዘዣ የሚባል ነገር ስለማይታወቅ በመንደሩ ለግርዛት የደረሱ ልጆች ቤተሰብ በአንድነት ተሰባስቦ ድል ያለ ድግስ ይደገሳል፡፡ ይበላል፣ ይጠጣል፣ ይጨፈራል፡፡ እስከ እኩለ ለሊት ድረስ የሚገረዙ ልጆችም እየበሉ ከጠጁም እየጠጡ እንዲጨፍሩ ይደረጋል፡፡ በጭፈራውና በመጠጡ ሲደክሙ ገራገፑ የግርዛት ተግባሩን ይፈፅማል፡፡ መብል፣ መጠጡና ጭፈራው እንደማደንዘዣ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የግርዛት ተግባሩ ሌሊት እንደተጠናቀቀ ጠዋትም ድግሱና ጭፈራው ይቀጥላል፡፡ መገረዛቸውንም ለማብሰር የነገርኩህን ምሳሌያዊ አነጋገር በዘፈናቸው መሀል ጣልቃ እያሰስገቡ ያቀነቅናሉ፡፡

ዋነኛ መልዕክቱ መገረዙን የሚገልፅ ነው፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ ያልተገረዘ ወንድ እንደወንድ አይቆጠርም፡፡ ማንኛዋም ሴት ልታገባውም ሆነ አብራው ልታድር አትሻም፡፡ ‹‹ yoochee bakee qooxoch tach beeroo yagiiti›› (በግራ ዶሮ ቆጥ በኩል ማደሪያ ላነጠፈችልኝ) እና ‹‹Yooxee shaatee goochochi bitoo tegiiti›› (በሰባራ ገል ጠጅ የቀዳችልኝን) ሲል ወንድ ሳይባል ተንቆ የቆየበትን ጊዜ ለመግለፅ ነው፡፡ በባህላችን ወንድና እንግዳ በአክብሮት በክብር ቦታ ይቀመጣል ያድራል እንጂ በስተግራ በኩል ጨርሶ አያድርም፡፡ ግራ እንስሳት ማደሪያ የሚሰራበት ነው፡፡ ያለመገረዙን ከእንስሳ ጋር ያዛምዱታል፡፡ ክብር የማይሰጠው መሆኑንም መጠጫውን ከገል ጋር ያያይዙታል፡፡

መገረዙንና ወንድ መሆኑን ‹‹qaana yagibebo iyee…xoofoo mayii beeboye ta anami bushoo anaameto tane iyee wene›› (በቀኝ በኩል አንጥፊ በኋት… ዋንጫ እጠቢ በኋት እኔ የወንዱ ልጅ ወንድ ሆኛለሁ፡፡) በማለት አያይዞ ይገልፃል፡፡ ይህንን የሚገልፀው የተገረዘው ወይም የተገረዙ ልጆች ሳይሆኑ አባቶች ወይም ወዳጅ ዘመዶች ናቸው ‹አሉ› እያሉ ሚናገሩት ወይም የሚዘፍኑት፡፡

ይህ በሁለተኛነት የቀረበው ምሳሌያዊ አነጋገር በይበልጥ ከወንድ ልጅ ግርዛት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብሔረሰቡ በዚህም ስነቃሉ ወይም ምሳሌያዊ አነጋገሩ ግራን ወይም ግራነትን እንደመጥፎ፣ እርኩስ፣ ከበሬታ የሌለውና የተናቀና ከወንድ ማይቆጠር አድርጎ ይመለከተዋል፡፡ በሁለቱም ምሳሌያዊ አነጋገሮች ውስጥ የግራኝነቱ ትርጉም የተንፀባረቀው በተመሳሳይ መልኩ ነው፡፡

ከዚህም ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡ ዘንድ ‹‹ዶነቴ ይባቶ›› በመባል በሚታወቀው ፌሊጣዊ አነጋገር ውስጥም ግራ ወይም ግራኝነት የተጣመመ፣ ግልፅ ያልሆነና የክፉ ተምሳሌትነት ያለው መሆኑን መረጃ አቀባይ ኢ.ምቶ ገብሬ (መጋቢት 15/ 2016) ገልፀዋል፡፡ ለዚህም ማሳያ

‹‹ne moyoo yoochone›› ⟶ ነገረህ ስራ)(ሽ) ግራ ነው፡፡ ግልፅነት የለውም

‹‹Yoocha nalayee›› ⟶ ግራ ፍርድ አትፍረድ(ጂ)፡፡ ሚዛናዊ (ፍትሃዊ) አይደለም

‹‹Qaana nalibee›› ⟶ ቀኝ ፍረድ(ጂ)፡፡ ሚዛናዊ (ፍትሃዊ) ሁን(ኚ) በማለት ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ በካፋ ብሔረስብ ስነቃል ውስጥ በዋናነት በሚት፣ በተረት፣ በምሳሌያዊ አነጋገሮችና ፌሊጣዊ አነገገሮች ውስጥ የግራኝነት ትዕምርትነት ወይም ዕሳቤን ከሰይጣናዊነት፣ ከእርኩስነት፣ ሚዛናዊ ወይም ፍትሃዊ ካለመሆን፣ ካለመታመንና ከመሳሰሉት አሉታዊ ነገሮች ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን መረጃዎች አሳይተዋል፡፡ በሚት ውስጥ ግራኝ የሰይጣን ቀኝ ደግሞ የፈጣሪ ተደርጎ መቅረቡ ብሔረሰቡ ለፈጣሪ ‹‹yeerii (yeero)›› ትልቅ ክብር ያለው መሆኑ ግራኝነትን ከክፋት ወይም ከሰይጣንነት ጋር እንዲያያይዝ መሰረታዊ ምክንያት ሆኖታል፡፡ ከመረጃ አቀባዮች የተሰበሰበው መረጃም ይኼንኑ ሀሳብ ያጠናክራል፡፡

## 5.5. የግራኝነትና ከእምነትና ወደፊት ዕድል ትንቢያ አንፃር

በሀገራችን በርካታ ማህበረሰቦች ዘንድ አንድ ሰው ወይም እንዲት ሴት ያለ ወትሮው (ያለወትሮዋ) የሚነጫነጭ (የምትነጫነጭ) ከሆነ (ከሆነች) ‹‹ምነው ዛሬ በግራ ጎንህ(ሽ) ነው እንዴ የተነሳኸው(ሽው)›› ማለት የተለመደ አገላለፅ ነው፡፡ በካፋ ብሔረሰብ ዘንድም ግራኝነት ከነገሮች መሳካትና አለመሳካት፣ ቀናነትና መጥፎነት ጋር በተያያዘ መልኩ

የሚሰጠው የራሱ የሆነ ትረጉም አለው፡፡ ይኼንን መነሻ በማድረግም ብሔረሰቡ ግራኝነትን መሰረት በማድረግ ወደፊት ሊገጥመው የሚችለውን ነገር በምን መልኩ ይተነብያል? ተብሎ ለመረጃ አቀባዮች በቀረበው ጥያቄ ከቦንጋ ዙሪያ የተመረጠው መረጃ አቀባይ አቶ አጦ ገብሬ (የካቲት 8/ 2016) የሰጠው መረጃ (ማብራሪያ) እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

> በእኛ በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ማለዳ በር ሲከፈት ከፋቹ ወንድም ይሁን ሴት የበሩን መወርወሪያ (qoocheeletoo) የሚነቅለው ወይም የምትነቅለው በቀኝ እጅ ነው፡፡ ከዚያም መወርወሪያው የሚንጠለጠል ከሆነ በማንጠልጠል አልያም ከቀኝ እጅ ወደግራ እጅ በማዘዋወር በሩን በቀኝ እጁ (እጇ) ይከፍታል (ትከፍታለች) እንጂ በር ወይም በብሔረሰባችን አጠራር ‹‹ጊፎ›› በግራ እጅ አይከፈትም፡፡ ከቤትም ግራ እግር ቀድሞ እንዲወጣ አይፈቀድም፡፡ አስቀድሞ ቀኝን ከዚያም ግራን ነው፡፡
>
> በግራ እጅ በር ቢከፈትና ግራ እግር አስቀድሞ ከቤት ቢወጣ ያሰቡት አይሳካም፤ ጥሩ እድል አይገጥምም ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑንም ባህላዊ የጎጆ ቤቶች አሰራር ይህንን ከግዛቤ ያስገባ ነው፡፡ በሩ ወይም ‹‹ጊፎ›› ከቀኝ ወደግራ እንዲከፈት ተደርጎ ነው የሚሰራው፡፡
>
> ከመረጃው ለመረዳት እንደሚቻለው በግራ እጅ በር ከተከፈተ ቀኑ ጥሩ አይሆንም ተብሎ ይታመናል፡፡ እርሻ የሚሄደውም ገበሬ ያሰበውን ያህል ሳያርስ የልቡን ሳያደርስ ይውላል፡፡ ለሌላ ጉዳይ የሄደ ሰውም ጉዳዩ ሳይፈፅምለት ይውላል ተብሎ ስለሚታሰብ በር በግራ እጅ አይከፈትም፡፡ አባወራም ሆነ ማንኛውን የቤቱ ቤተሰብ ከቤት ሲወጣና ሲፀልይ በፀሎቱ መሃል ‹‹qaana ta hheechibe›› ‹‹በቀኝ አውለኝ›› የሚል ቃል አይጠፋም፡፡ ከዚህ በመነሳትም ግራ የመጥፎ ወይም አሉታዊ ነገር የሚያስከትል ተብሎ የሚታመን መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ እምነት በብሔረሰቡ ዘንድ ከተለያዩ ተቋማዊ እምነቶች መስፋፋት አስቀድሞ እንደነበረም የሚከተሉት መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

የካፋ ብሔረሰብ የራሱን ሀገረሰባዊ ሀይማኖት ለበርካታ ዘመናት ሲያራምድ የቆየና አሁንም በማራመድ ላይ የሚገኝ ብሔረሰብ ነው፡፡ በሀገራችን በስፋት እውቅና ያላቸው የክርስትና፣ የእስልምና፣ የፕሮቴስታንትና የሌሎች ሀይማኖቶች ከመስፋፋታቸው በፊት የካፋ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ ሀገረሰባዊ ዕምነት በንጉሳዊ ዘመን እንደነበረው መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

In Southwest-Ethiopian Kafa society, the widely practised belief in *eqo*, a form of worship of the god *Yeero*, was conducted through the *alamo* (diviner), a medium who was believed to com-municate with the spirits. This tradition was inseparable from the politics, economy, and society of the Kafa Kingdom, which prospered from the mid-14th century to 1897. Following its con-quest by and incorporation into the Ethiopian Empire, the Kafa society was introduced to Ethiopian Orthodox Christianity, and many converted to the faith. Nonetheless, the deeply rooted belief in *eqo* continued to exert a great influence on the Kafa people, who would visit the *alamo* while also visiting the church. However, under the Derg regime, all religious activities were regulated, and it was dificult to openly practise the *eqo* traditions (Sayuri 2021፤ 1)

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኘው የካፋ ብሔረሰብ ጥንታዊ የሆነ ስርዓተ ዕምነት ያለው ብሔረሰብ ነው፡፡ ብሔረሰቡ ‹‹ኤቆ›› የተባለን ‹‹ዬሮ›› እንደፈጣሪ የሚመለክ ሲሆን አማላጅ ወይም የእምነቱ መሪዎችም ‹‹አላሞ›› ወይም ቃልቻዎች ናቸው፡፡ ይህ እምነት በብሔረሰቡ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም የንጉሳዊ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ አመነታ ያለው ነው፡፡ እምነቱም በብሔረሰቡ ንጉሳዊ አስተዳደር ስርዓት ከ14ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 1897 ድረስ ማለትም በአፄ ሚንሊክ አገዛዝ ስር እስከሚወድቅ ድረስ በንጉሳዊ አስተዳደር ስር ዕምነቱ ይከበር ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ የክርስትና እምነት መስፋፋትና በደርግ ዘመነ መንግስት ወቅት ስርዓተ አምልኮውን ‹‹ኤቆ›› በግልፅ ማክበር አዳጋች ሆኗል፡፡

የሳውሪ ጥናታዊ ፅሑፍ በዋናነት ትኩረት ያደረገው ሀገረሰባዊ ዕምነት የሆነው ‹‹ኤቆ›› ላይ ሲሆን ይንን መነሻ በማድረግም የካፋ ብሔረሰብ ዕምነት እንደነበረና አሁንም ያለ መሆኑን የክርስትናና እስልምና እምነቶች እንዲሁም የካቶሊክ እምነት ከ‹‹ኤቆ›› አንፃር ሲታዩ በብሔረሰቡ ዘንድ የቅርብ ዘመን መሆናቸው ይጠቁማል፡፡

በብሔረሰቡ የ‹‹ኤቆ›› አምልኮ ስርዓት ‹‹አላሞ›› ወይም ቃልቻዎች ባላቸው የመንፈስ አራማጅነት የተለያየ እርከን እና የተለያየ ስያሜ እንዳላቸው የገሊላ ሀብተማሪያም (2021፤31) አሳማኝ ማመሳከሪያ ወይም ማሳያ ነው፡፡ አጥኚዋ ‹‹ Damochechi›› (ዳሞቼቺ) በጨና አካባቢ፣ ‹‹Yaferochi› (ያፌሮቺ) እና ‹‹ Wogidochi›› (ወጊዶቺ) በአዲዮና ሸራዳ አካባቢ፣ ‹‹ Asheellochi›› (አሼሎቺ) በመላው ካፋ አካባቢ፣ ‹‹ Gaara-maanji or Gaara maanjoochi ›› (ጋራማንጂ) በታወቁ ቤንች አካባቢዎች እና ‹‹Dochi or De'e-taateeno››(ዶቺ ወይም ደኤ ታቴኖ) በመላው የካፋ አካባቢ የሚመለኩ ሀገረሰባዊ ዕመነቶች እንደሆኑ በጥናቷ አመላክታለች፡፡

በሀገረሰባዊ ዕምነት አምልኮ ስርዓት መስዕዋት በሚቀርብበት ወቅት እንዲሁም አንዳንድ ስርዓቶች በሚካወኑበት ወቅት ቀኝና ግራኝ እጆች ወይም የሰውነት ክፍሎች የተለያየ ትርጓሜ አላቸው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ሻኛቸው ወደግራ የወደቀናኳክኑ ወይም ኮከኑ ወደግራ የደፋ አውራ ዶሮ ለ‹‹ኤቆ›› ወይም ለሌች ስርዓተ አምልኮዎች በምስዕዋትነት አይቀርብም፡፡

ከካፋ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ ዕምነቶችና አምልኮዎች መካከል አንዱ ‹‹ቆሌ ዴጆ›› ነው፡፡ ቆሌ ዴጆ አዝመራ ተሰብስቦ ከገባ በኋላ የሚከናወን ስርዓተ አምልኮ ወይም ከበራ ሲሆን አዲስ ከተሰበሰበው እህል የተለያዩ ምግቦችን በማዘጋጀት እህሉን ጠብቆ ላደረሰ አድባር መስዕዋት ሚቀርብበት ሂደት ነው፡፡ በሂደቱም መስዕዋት አቅራቢው መስዕዋቱን ለአድባሩ በግራ እጁ አያቀርብም፡፡ መስጠት ያለበት በሁለት እጁ ነው፡፡ ካልሆነ በቀኝ እጁ፡፡ መስዕዋት ከሚታረደውም ዶሮ ቀኝ ክፍሉን ለአድባር ወይም ‹‹ቆሎ›› ይሰጣሉ፡፡ ይንን አስመልክቶ ሰለሞን (2013) የሚከተለውን መረጃ አስፍሯል፡፡

> ‹‹…በመቀጠልም ከዶሮዉ አካላት ቀኝ ክንፉን፣ ሁለቱ እግሮችን፣ ጭንቅላቱንና ላባዉን በአንድ ላይ በተቀጣጠለዉ እሳት ላይ ይጨምሩና ያቃጥላሉ፡፡ ለቆሎ ቀኝ ጎን ወይም ቀኝ ክንፍ የሚሰጠዉ መልካሙን ሁሉ ለአንተ ከማድረግ ወደኋላ አልልም ከሚል እሳቤ ነዉ፡፡ በአካባቢዉ ማህበረሰብ ዘንድ ቀኝ የመልካም ነገር ምልክት ነዉ፡፡ አርሶ አደሩም ሆነ ማንኛዉም የአካባቢዉ ማህበረሰብ ማለዳ ከእንቅልፉ ሲነሳ ‹ቃና ታን ሂቺብ› (በቀኝ አዉለኝ) ብሎ መጸለይ የተለመደ ነዉ፡፡›› (ሰለሞን 2013፣ 28)

በመሆኑም በካፋ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ ዕምነትና አምልኮ ግራኝነት ከእርኩስነት ወይም ከሰይጣንነት ጋር ተያይዞ ይታያል፡፡ በአንፃሩ ቀኝ የተቀደሰና የመልካም ተምሳሌት ተደርጎ በብሔረሰቡ ዘንድ ይወሰዳል፡፡

## 5.6. ግራኝነት በግብይት ሂደት ውስጥ ያለው ትዕምርትነት

በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ገንዘብ በግራ እጅ መስጠት ትልቅ ነውር ነው፡፡ በተለይ አንድ ግለሰብ ከብት ወይም በግ አሊያም ዶሮ ወደገበያ ይዞ እየሄደ ገበያ ውስጥ ሳይገባ ገዢ ሲጠይቀውና ገበያ ውስጥም ገብቶ የመጀመሪያ ጠያቂ ወይም ገዢ ሲመጣ ‹‹gijjoo ta yechiib›› ‹ገንዘብ አስይዘኝ› የሚባል ነገር አለ፡፡ ይህም ማለት ‹ገና ገበያ እየወጣሁ ነውና በደረቁ ዋጋ ብቻ ሰምተህና ነግረህ እኔንም በደረቁ እንዳታውለኝ እጀ እርጥብ ሆነህ እኔም

ደስተኛ እንድሆን ገንዘብ አስነካኝ› (ገድ በለኝ) ማለት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ገገርው ዋጋው ከመጠራቱ በፊት ብር አውጥቶ ሻጩን ያስይዘዋል ወይም ያስነካዋል፡፡ በዚህ ወቅት ገገርው ገንዘቡን በግራ እጁ አውጥቶ በግራ እጁ ለሻጩ ቢዘረጋለት መጥፎ ዕድል እንደተመኘለት ይቆጠራል፡፡ በሻጩ ዘንድም ገገርው ‹‹ላፊ›› ወይም ‹‹ሰይጣን›› ተደርጎ ይሳላል፡፡

በብሔረሰቡ ዘንድ በግብይት ሂደት ለሚፈፀም ክፍያ ገንዘብ በግራ እጅ አይሰጥም፡፡ ተቀባዩም በግራ እጁ አይቀበልም፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ‹‹በግራ እጅ የተሰጠ ገንዘብ በረከት የለውም›› ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ይህ ተግባር ከስልጣኔ ጋር ተያይዞ በከተማው አካባቢ ማለትም በቦንጋ ከተማ አካባቢና በአንዳንድ የወረዳ ከተማዎች እየቀረ የመጣ ቢሆንም የገጠራማው አካበቢ ህብረተሰብ ግን ይህ እሳቤ አሁንም ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡

## 5.7. ግራኝነት በአመጋገብ ስርዓት ውስጥ ያለው ትዕምርትነት

በሀገራችን በሚገኙ በርካታ ማህበረሰቦች በግራ እጅ መመገብ የተለመደ አይአለም፡፡ አንዳንዶች ከእምነት አስተምህሮ አንፃር ሲመለከቱት ሌሎች ደግሞ በልምድ በቀኝ ይመገባሉ፡፡ በክርስትናው አስተምህሮ በግራ መመገብ በረከት የሚያሳጣ መሆኑን እንዲህ ይገልፃል፡፡ *‹‹ሰው በቀኙ በኩል ይነቅላል ይራብማል በግራም በኩል ይበላል አይጠግብምም እያንዳንዱም የክንዱን ስጋ ይበላል (ትንቢተ ኢሳያስ 9፡20)* ተብሎ ተገልጿል፡፡

በካፋ ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ቦታ ከሚሰጣቸው ማህበራዊ መስተጋብሮች መካከል አንዱ አብሮ መብላት ነው፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ አብሮ መብላት ወይም ማዕድን በጋራ መካፈል የመተሳሰብን፣ የወንድማማችነትን ወይም የዝምድና ትስስርን የመፍጠር ያህል የሚቆጠር ጠንካራ መስተጋብር ነው፡፡ ታዲያ በዚህ መስተጋብር ውስጥ የራሱ የሆኑ ሂደቶችና ክንውኖች አሉ፡፡

በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ በማዕድ ላይ በግራ እጅ መብላት ወይም መመገብ በጣም ከባድ ነውር ነው፡፡ ይህን አስመልክቶም አቶ አስፋው (መጋቢት 7/ 2016) እንዲህ ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

> በባህላችን መሰረት በግራ መብላት ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ በጣምም ነውር ነው፡፡ ለምን ቢባል ከግራኝ ሰው ጋር ሰው አብሮ ከበላ አይጠግብም፡፡ በረከትም የለውም፡፡

> ስለዚህ በልቶ ከማይጠግብና በረከት ከሌለው ሰው ጋር ማንም አብሮ መመገብን አይፈልግም፡፡ አንዳንዶች እንዲያውም አብሯቸው ወደ ማዕድ የቀረበው ሰው ግራኝ ከሆነ ማዕዱን ለብቻው ጥለውለት ሊነሱ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ በግራ መመገብ ነውር ነው፡፡

ከዚህ መረጃ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፤ በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ በግራ እጅ መመገብ ከነውርም ባለፈ እስከ መገለል ደረጃ የሚያደደርስ ነው፡፡ በመሆኑም በብሄረሰቡ ዕምነት መሰረት ግራኝ የሆነ ሰው በልቶ የማይጠግብ፣ በረከት የራቀው እንዲሁም ከሰይጣን ጋር አብሮ የሚመገብ ተደርጎ የሚታሰብበት ሁኔታዎች እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## 5.8. ልጆች ግራኝ እንዳይሆኑ የሚደረግ ክልከላ

ግራኝነት የሰይጣንነት ወይም የመጥፎ እድል ተምሳሌት መሆኑን ቀደም ሲል ከቀረቡት መረጃዎች አይተናል፡፡ በመሆኑም ወላጆች ልጆቻቸው ግራኝ እንዳይሆኑ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋሉ፡፡ በተለይ እናቶች ሴት ልጆቻቸው ግራኝ እንዳይሆኑ ጥብቅ ክትትል ያደርጋሉ፡፡ ምክንያቱም ለትዳር ማንም አይፈልጋትም ወይም ቤት ውስጥ በግራ ብትሰራም በረከት የላትምተብሎ ስለሚታሰብ እንደሆነ ቀደም ሲል አንስተናል፡፡ ልጆች ግራኝ መሆን አለመሆናቸውን የመለየት ሂደትንና ግራኝ ከሆኑ በግራ መጠቀም ትተው በቀኛኛቸው እንዲጠቀሙ ለማድረግ የሚደረጉ ቅጣቶችን አስመልክቶ አቶ ክፍሌ ወ/ማሪያም (መጋቢት 7/ 2016) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ልጆች ግራኝ መሆን አለመሆናቸው የሚለየው ገና በልጅነታቸው ነው፡፡ ወንድ ከሆነ ገና በልጅነቱ አባትየው ድንጋይ ወይም እንጨት በመስጠት እንዲወረውር ያደርገዋል፤ በየትኛው እጅ እንደወረወረም ያስተውላል፡፡ ምግብ ለብቻው እንዲሰጠው ይደርግና በየትኛው እጁ እንደሚበላም ያጤናል፡፡ ሴት ልጅንም እናት እንዲሁ የተለያዩ ስራዎችን ስትሰራ በየትኛው እጅ እንደምትሰራ ትከታተላለች፡፡
>
> ልጆቹ ግራ እጃቸውን የሚጠቀሙ ከሆነ በመጀመሪያ በቀኝ እጃቸው እንዲሰሩና እንዲበሉ ይመክሯቸዋል፡፡ ግራን እጃቸውን መጠቀም ካላቆሙ አሳቻ ሰዓት እየጠበቁ በቁንጥጫ ወይንም በግርፊያ ለማስተካከል ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ሂደትም ካላስተካከሉ ምግብ በሚመገበበት ወይም በምትመገብበት ወቅት ግራ እጃቸው ከክንዳቸው ጋር ተጣብቆ ይታሰራል፤ ወይም የግራ እጃቸውን አውራ ጣት

መዳፍ በምላጭ ወይም ስለታም በሆነ ነገር ይቆርጡታል፡፡ ህመሙ ለተወሰነ ጊዜ ስለሚቆይ ግራ እጃቸውን ትተው ቀኝ እጃቸው መጠቀም ይጀምራሉ፡፡ በአሁን ወቅት ግን እንደነዚህ አይነት የመግቻ ቅጣቶች ቀርተዋል፡፡

የብሔረሰቡ ስነቃልም ሆነ ሀገረሰባዊ እምነቱ ግራኝነትን የወከለበት ትርጉም አሉታዊና የማይደገፍ በመሆኑ አብዛኛዎቹ ልጆች  ቀኝ እጃቸውን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርገው ያድጋሉ፡፡ ግራን እንዳይመርጡ የአካባቢው ተፅዕኖ የጎላ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም በልጆች ተግባር ሂደት ውስጥ የግራና የቀኝ እጅ መረጣ ላይ የማህበረሰብ ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

እድገት በአብሮነትና ነገሮችን ወይም የማህበረሰቡን ዕሴት የመማር ሂደት በአብሮነት መስተጋብር ውስጥ የሚገኝ እንጂ በአንድ ግለሰብ ብቻ የሚከናወን ተግባር አይደለም፡፡ አንድን ግለሰብ የሚቀርፀው ማህበረሰቡ ነው፡፡ በመሆኑም በካፋ ብሔረሰብ ልጆች ከግራ ይልቅ ቀኝን እንዲመርጡት ማህበረሰቡ የራሱን የሆነ ተፅዕኖ እንደሚያደርግ መረጃው ያሳያል፡፡

እንደአጠቃላይ ሲታይ የካፋ ብሔረሰብ ግራኝነትን ወይም ግራን ከሰይጣንነት ጋር ያያዘ በመሆኑ ግራኝ የሆኑ የብሔረሰቡ ክፍሎች እንዲሁም አካላቸው ከግራኝነት ጋር ተያይዞ የተለያየ ትርጓሜ የሚሰጣቸው እንስሳት ኢ-ፍትሃዊ የሆኑ፣ መጥገብ ወይም ማጥገብ የማይችሉ፣ በረከት አልባዎች፣ ተንኮለኛዎች፣ የበታች የሆኑና መልካም ነገር የሌላቸው ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ ይህ አመለካከት ይበልጥ በብሔረሰቡ ዘንድ እንዲሰርፅ የብሔረሰቡ ስነቃሎች ትልቁን ሚና ተጫውተዋል፡፡ በአሁን ጊዜም ቢሆን ከላይ የተዘረዘሩትን የግራ ትዕምርታዊ ፅንሰ ሀሳቦች ብሔረሰቡ እንደባህል እያስቀጠለው ይገኛል፡፡ ነገር ግን ልጆች ግራኝ እንዳይሆኑ የሚደረገው ክልከላ አካላዊ ቅጣቱ ሙሉ ለሙሉ ሚባል ደረጃ ቀርቷል፡፡ ከዚህ ባሻገርም በትዳር ውስጥም ግራ የሆነች ሚስት ሰርታ አታጠግብም የሚለው ስርዓትም እየቀረ መጥቷል፡፡

## 5.9. ግራኝነት በስነልቡና ላይ የሚኖረው አንድምታ

ስነልቦና መሰረት የሚያደርገዉ በሰዉ ልጅ አዕምሮ ላይ እና ስዕብናዉ ላይ ነዉ፡፡ በመሆኑም ስነልቦና የሰዉን ልጅ አዕምሮ እድገት ከጨቅላነት እስከ ህጻንነት ብሎም እስከ

አዋቂነት ደረጃ ያሉትን ሂደቶች እንደሚያካትትም የስነልቦና ተመራማሪ የሆነዉ ሲግመንድ ፍሮይድ ይገልጻል፡፡ እንደ ፍሮይድ ገለጻ

በአብዛኛዉ ምሁራን እይታ በሰዉ ስዕብና ዉስጥ ከጨቅላነት እስከ ህፃንነት ከዚያም ሙሉ ሰዉነት ድረስ አዕምሮ የሚመራባቸዉ ክፍሎች እንዳሉና እነዚህም ክፍሎች ኢድ፣ ኢጎ እና ሱፐር ኢጎ ይባላሉ፡፡ የስነልቦና መሰረቱ የሰዉ ልጅ ነዉ፡፡ የሰዉ ልጅ ደግሞ ከሌሎች ህይወት ካላቸዉ የሚለየዉ ላቅ ያለ የአስተሳሰብ ደረጃ ባለቤት መሆን መቻሉ ነዉ፡፡ የአስተሳሰቡ መሰረት ደግሞ አዕምሮዉ ነዉ፡፡ በመሆኑም በእድገት ሂደቱ ወቅት ስነልቦናዉ ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያጋጥመዉ ይችላል፡፡ ይህንን አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚያትትልን ሳይንስ ደግሞ ስነልቦና ይባላል፡፡

በህፃናትም ሆነ በትላልቅ ሰዎች ላይ የአካላዊ ቅጣት እርጃ መውሰድ በቅጣት ተቀባዩ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖን ያሳድራል፡፡ በዚህ መሰረትም ልጆች ግራ እንዳይሆኑ የሚቀጡት ቅጣት በህፃናቱ አካል ላይ ብቻ ሳይሆን አዕምሯዊ ዕድገት ላይ ተፅዕኖ ያስከትላል፡፡ የተደረገው ክልከላ በራስ መተማመናቸውን በመናድ ግራ እጅ ከቀኝ እጅ እኩል ሚና የሌለው እንዲመስላቸው ያደርጋል፡፡ በመሆኑም በህፃናት አዕምሮ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖን ይፈጥራል፡፡

በሁለተኛ በግራ እጅ ማዕድ ላይ አይቀረብም፡፡ አንድ ግለሰብ ከሌሎች ጋር በአብሮነት እየተመገበ ግራኝ ከሆነ ማዕዱን ጥለውለት ይነሳሉ፡፡ ይህ ተግባር ግራኝ በሆነው ግለሰብ ላይ የመገለል፣ የበታች የመደረግ ማለትም እንደእርኩስ የመቆጠር ስሜትን ያሳድርበታል፡፡ ግራኝ በመሆኑ እንዲያፍር ያደርገዋል፡፡ ይህም ተግባር በግለሰቡ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን ያሳድራል፡፡ በሌላ መልኩ አንዲት ሴት ግራ እጇን በይበልጥ ለማብሰልና ለተለያዩ ተግባራት መጠቀም መቻሏ ለትዳር እንዳትታጭ ማድረጉም በራሱ አሉታዊ ተፅዕኖን ያሳድራል፡፡ የአሉታዊ ተፅዕኖ ምንጩ ግራ እጅና ቀኝ እጅ ወይም ግራ የአካል ክፍልና ቀኝ የአካል ክፍል መበላለጥና ማነስ፣ መስነፍና መጠንከር፣ ማገልገልና አለማገልገል ሳይሆን ግራኝነትን ብሔረሰቡ በሀሳብ ደረጃ የሰይጣን ወይም የክፉት ተምሳሌት አድርጎ ትርጓሜ መስጠቱና በብሔረሰቡ ስነቃልና ሀገረሰባዊ እምነት አማካይነት ከትውልድ ወደትውልድ እያሸጋገረ መቀጠሉ ነው፡፡

በአንፃሩ ከስልቦና አንፃር ግራ ላልሆኑ አካላት ግራ አለመሆናቸውና ግራ ያልሆነ ነገር መስዕዋት አለማቅረባቸው መንፈሳዊ ደስታን እንዲቀዳጁ ያደርጋል፡፡ ሻኛው ወደግራ

ያልወደቀን በሬ ለአምልኮ ስርዓት መስዕዋት ማቅረቡ ወይም ማቅረባቸው ለፈጣሪያቸው የታመኑ መሆናቸውን ማሳያ በመሆኑ ጥልቅ ደስታን እንዲቀዳጁ ያደርጋል፡፡ በራስ መተማመናቸው እንዲያጎለብት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ ይህ ከስነልቦና አንፃር ሲታይ አዎንታዊ ገፅታ እንዲኖረው ያስችላል፡፡

## 5.10. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ተቀዳሚ ዓላማ የግራኝነት ማህበራዊና እምነታዊ ፍልስፍና በካፋ ብሔረሰብ ተተኳሪነት ብሔረሰቡ ግራኝነትን በምን አይነት ትዕምርትነት እንደሚገልፅ ተንትኖ ማሳየት ነበር፡፡ የካፋ ብሔረሰብ ግራን ከሰይጣን፣ ከመጥፎ አመለካት፣ ከአልጠግብ ባይነት፣ ከበረከት አልባነት፣ ከፍርደ ገምድልነት ወይም ከኢ-ፍትሃዊነት ጋር በማያያዝ ሰዎችን፣ እንስሳትንና አካላቸውን መነሻ በማድረግ ትርጎማ እንደሚሰጡ መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ በመረጃዎቹም መሰረት ግራኝነት የሰይጣንነት፣ የክፋት፣ የስግብግብነት ወይም የአልጠግብ ባይነት እንዲሁም በብሔረሰቡ ዘንድ በሚታመኑ ሀገረሰባዊ ዕምነቶች አንፃር የእርኩስነት ትዕምርትነት ያለው መሆኑን መረጃዎች አመላክተዋል፡፡

በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት ተዛማጅ ጥናቶች አንፃር ሻንሹና ሌሎች (2022) ግራኝነትን ከአንድ በጋና ጋባን ጆንግ ብሔረሰብ አንፃር ለመፈከር ያደረጉት ሂደት ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ከግኝት አንፃር በብሔረሰቡ ዘንድ ያለውን የሀገረሰባዊ እምነት ተፅዕኖና ሚና እንዲሁም የሰይጣንነት ትዕምርትነትን የማይገልፅ መሆኑ ልዩነት እንዳለው ያመላክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ግራኝነት በጋና ጋባን ጆንግ ብሔረሰብ ውስጥ ያለው ትርጓሜ አለማቀፋዊ ይዘት እንዳለው አመላክተዋል፡፡ የካፋ ብሔረሰብ ግራኝነትን በአሉታዊነት መተርጎሙ ከተወሰኑ የዓለም ክፍሎች እሳቤ ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በካፋ ብሔረሰብ ከተሰበሰቡት የስነቃል ሀብቶች በሚት፣ በተረት፣ በምሳሌያዊ ንግግርና በፈሊጣዊ አነጋገር ውስጥ ግራኝነት የተለያ ትዕምርትነትን ይዞ መቅረቡን በገለጻው ክፍል፤ በሚት ውስጥ - ግራኝነት የሰይጣን መሆንን፤ በተረት ውስጥ - ግራ የስውር ተንኮል፣ በምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ - የአቅመቢስነትን ወይም የአለመታመንና የርኩስ ወይም የመናቅ እንዲሁም በፈሊጣዊ አነጋገር ውስጥ ደግሞ የኢ-ፍትሃዊነት ትዕምርትነት ይዞ ቀርቧል፡፡

ከላይ የቀረበው የግኝት ውጤት በተዛማጅ ጥናት ቅኝቶች ላይ በተዳሰሱ ጥናቶች ላይ ያልተመላከተ ወይም አጥኚዎች ትኩረት ያላደረጉበት ውጤት ነው፡፡ የስነቃል አይነቶችን መሰረት አድርጎ የቀረበው የግኝት ውጤት በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ግራኝነት ከትዕምርትነት በ‹‹THE ENCYCLOPEDIA OF WORLD PROBLEMS& HUMAN POTENTIAL›› (symbolic) የተገለፀውን ብያኔ የሚያመላክት ነው፡፡

ብሔረቡ ግራኝነትን በመጥፎ ተምሳሌትነት ወይም ትዕምርትነት እንዲወስድ ተፅዕኖ እንዲኖር በዋናነት ያስቻለው ስነቃዊ እሴቶች ተፅዕኖና የሀገረሰባዊ ዕምነት አስተምህሮ ተፅዕኖ እንደሆኑ በገለፃው ክፍል ተመላክቷል፡፡ ከእምነት አስተምሮ አንፃር ከክርስትና እምነት፣ ከእስልምናውና ከሌላው የእምነት አስተምህሮ ቀደምት እንደመሆኑ ፣ ግራኝ አልሞ የማይስት መሆኑን መፅሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ገልፆታል፡፡

*‹‹ከዚያም ሕዝብ ሁሉ ሰባት መቶ የተመረጡ ግራኝ ሰዎች ነበሩእነዚህም ሁሉ ድንጋይ ይወነጭፉ ነበር አንድስ ጠጉርስ እንኳ አይስቱም›› (መፃፈ መሳፍንት 20፣16)*

የካፋ ብሔረሰብም ከላይ እንደተገለፀው ግራኝ ሰዎች አልመው የማይስቱ መሆናቸውን ያምናል፡፡ ነገር ግን በውትድርና ስርዓት ውስጥ ያለመካተታቸው አልሞ መምታት እምነታዊ አስተምህሮ መሰረት ቢኖረውም ለሹመትና ለሌሎች ወታደራዊ ስልጣናት አለመመረጥ ማህበራዊ ዕሳቤ ላይ መሰረት ያደረገ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ Alhassan (2017) በጥናቱ ግራ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ መቶ ጊዜ በአሉታዊነት ሃያ አምስት ጊዜ በአዎንታዊነት መነሳቱን ማመላከቱ ተገልጿል፡፡ ከተሰበሰቡት የካፋ ብሔረሰብ ስነቃሎችና ዕምነታዊ ትንተናዎች ግራ በአዎንታዊነት ሊገለፅ የሚችል ሁዳይ አለመኖሩን በመፅሐፍ ቅዱስ አልሞ አለመሳት አዎንታዊ ገፅታ ሊኖረው ይችላል፡፡ በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ አልሞ አለመሳት የክፋት ወይም የመጥፎ አጥቂነት ትርጓሜ እንዳለው የጥናቱ ውጤት ትርጓሜ ያሳያል፡፡

ሚት የግራኝነት እሳቤ ብሔረሰቡ ከሰይጣንነት ጋር ተያይዞ ትልቁን ሚና የተጫወተ መሆኑን ከመረጃዎቹ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከክርስትናና እስልምና እንዲሁም ከሌሎች እምነቶች መስፋፋት በፊትም ይህ ሚት መኖሩ ማህበራዊ አስተሳሰብ ወይም ፍልስፍና ላይ ይበልጥ መሰረት የጣለ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የብሔረሰቡ አባላት ግራኝነትን ከሰይጣንና ከክፉ ስራ ጋር ማያያዛቸው ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ አሉታዊ እሳቤ እንዲይዝ አድርጎታል፡፡ አሉታዊነቱንም ህፃናት ግራኝ እንዳይሆኑ ጥብቅ ክትትልና ሲሆኑም የከፋ ቅጣት እስከማስከተል እንደሚደርስ በገለፃው ክፍል ቀርቧል፡፡ ይህ በታደጊዎች ስነልቦና ላይ የሚያሳድረው ጫና ቀላል አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከአካላዊ ቅጣቱ ይበልጥ ግራኝ የሆነ ሰው ከመዐድና ከሌሎችም ማህበራዊ ግንኙነቶች የሚደርስበት መገለል የሚያሳድረው ስነልቦናዊ ጫና ቀላል አይደለም፡፡ ፍሮይድ መገለልን የሚፈጥሩ አጋጣሚዎች በአንድ ግለሰብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በአዕምሮውና ስዕብናው ላይ እንደሚፈጥር ‹‹ስዕብናና የሳይኮ አካዳሚክስ እይታ›› በሚል ንድፈ ሀሳቡ ስር ገልፆታል፡፡ የካፋ ብሔረሰብ ግራኝነት ላይ መሰረት ያደረጉ ማግለሎችም የፍሮይድን ሐሳብ የሚያጠናክሩ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 6.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በዋናነት ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ማህበራዊና እምነታዊ እይታ አንፃር ያለውን ትዕምርትነት ከአጥኚው ግለ ገጠመኝና የብሔረሴቡን የግራ ትዕምርትነትን ከማጥናት ፍላጎት እንዲሁም አጥኚዎች ግራኝነትን መሰረት አድረገው ባካሄዱት ጥናቶች ላይ የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት በመነሳሳት መረጃዎችን በመሰብሰብ ገላጭ ትንተና አካሂዷል፡፡ ልጥናቱ የካፋ ብሔረሰብ የግራኝነት ማህበራዊ ትዕምርትነትን ከሀገረሰባዊ ዕምነትና ከብሔረሰቡ ስነቃል አንፃር የመመረመረ ነው፡፡ ጥናቱ ግራኝነት በብሔረሰቡ ዘንድ ያለውን ትዕምርትነት ፍከራዎችን ከእንስሳት አካል አፈጣጠር፣ ከማህበራዊ መስተጋብር፣ ከብሐረሰቡ ሀረገረሰባዊ እምነት፣ ስነቃል አንፃር፤ ከሚልኪ አንፃር በተዳሰሰበት ወቅት ብሔረቡ ግራን በአሉታዊነት የሚመለከት መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ህፃናት በእድገት ወቅት ግራኝ እንዳይሆኑ የሚደረጉ ክልከላዎችና ከፍ ሲልም ቅጣቶች እንዲሁም ግራኝ የሆኑ ከተለያዩ ማህበራዊ መስተጋብሮች የሰይጣንነት ወይም ፍርደ ገምድልነት ትርጓሜ ተላብሰው መገለላቸው ለአሉታዊነት አመለካከቱ ማሳያ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅትም ሆነ ከዚህ ቀደም ብሔረሰቡ ግራኝነትን ከአሉታዊ ነገሮች ጋር የሚያያይዝበትን ሂደት መሰረት በማድረግ ‹ለምን ?›› ለሚል ጥያቄ ‹‹ነውር ነው ወይም ባህል ነው፡፡›› የሚሉ ድፍን ያሉ ምላሾችን ከመስጠት በስተቀር ባህላዊ ወይም እምነታዊ ትዕምርትነቱን በውል አይገነዘቡትም፡፡ በመሆኑም በብሔረሰቡ ዘንድ ግራን ወይም ግራኝነትን መሰረት ያደረጉ ክልከላዎች ከእምነት አንፃር ጥንታዊነት ይዘት ያለው ሀገረሰባዊ ዕምነት ወይም ‹‹ኤቆ›› እና ስነቃላዊ እሴቶች በበይበልጥ ሚት፣ ተረት፣ ምሳሌያዊ አነጋገርና ፈሊጦች ተፅዕኖ እንዳላቸው ከላይ በቀረበው መረጃ ተመላክቷል፡፡ ሀገረሰባዊ ዕምነቱና ስነቃሉ መሳ ለመሳ መጠናታቸው ፋይዳው የጎላ መሆኑንም ጥናቱ ማሳያ ነው፡፡የሀገረ ሰባዊ እምነቶቹ መጠናት እምነቶቹን የሚከውናቸው ማህበረሰብ ያለውን የህይወት ፍልስፍና፣ የአኗኗር ዘዬ፣ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈ ያቆያቸውን የህይወት ዘመን ልማዶች፣ ጥበቦች ወዘተ ...ያላቸውን ትርጓሜ፣ ማህበራዊ

ፋይዳና ምንጫቸውን ወዘተ… ሰንዶ በማስቀመጥ ለቀጣዩ ትውልድ ከማሸጋገርና በትውልዱ አእምሮ ውስጥ ጥያቄ ለሚያጭሩ ጉዳዮች ምለሽ እንዲያገኝ ማስቻል የአካባቢው ብሔረሰብም ሆነ ሌሎች ብሔሰቦች ስለብሔረሰቡ ባህል በቂ እውቀት እንዲይዝ ማስቻል ተገቢ ነው፡፡

## 6.2. አስተያየት

በሀገራችን የተለመደው አብይ የፎክሎር ዘርፎች ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ ላይ ነው፡፡ በተከለመዱና በተዘወተሩ ቃላዊ፣ ቁሳዊ፣ እምነታነዊና ትውን ጥበባዊ ጉዳዮች ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ ጥቃቅን የፎክሎር ቅንጣቶች የአንድን ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ዕምነታዊና የመሳሰሉ ዕሳቤዎችን መግለጥ እንደሚችል ይህ ጥናት በመጠኑም ቢሆን አመላካች ነው፡፡ በትውልዱም ዘንድ ለሚፈጠረው አመክኖአዊ ጥያቄዎችም በቂ ምላሽ ለመስጠት ከተተኮሩት ይልቅ ያልተተኮሩ ማህበራዊ እሴቶች ላይ ምርምር ማካሄድ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

ይህ ጥናት በዋናነት ብሔረሰቡ ግራኝነትን ከተለያዩ እሳቤዎች አንፃር ትዕምርት መተንተንና መተርጎም ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ የብሔረሰቡ የግራኝነት ትርጓሜ ከሁለት አቅጣጫዎች አንፃር የሚታይ ነው፡፡ አንደኛው አካባቢያዊ ወይም ማህበራዊ ትርጓሜ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አለማቀፋዊ ወይም ሁለንተናዊ ትርጓሜ ነው፡፡ ይህ ጥናት በስፋት አካባቢያዊ ወይም ማህበራዊ ትርጓሜ ላይ መሰረት ያደረገ መሆኑን ከላይ የቀረቡ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በስፋትና በጥልቀት ሀገራዊና አለማቀፋዊ አድምታው አልተዳሰሰም፡፡ በመሆኑም የብሔረሰቡ የግራኝነት ትርጓሜ ከሌሎች ብሔረሰቦችና ከአለም አቀፋዊ ትርጓሜ አንጻር ቢጠና ከሌላው ጋር ያለውን የሁለንተናዊ ተዛምዶና ልዩነት የማሳየት አቅም ስለሚኖረው ከዚህ አንጻር ሌሎች ጥናቶች ቢካሄዱ መልካም ይሆናል፡፡

ግራኝነት በካፋ ብሔረሰብ ዘንድ ያለው ትዕምርትነት ባህላዊና ዕምነታዊ ዳራ እንዲሁም ማመሳከሪያ ሀሳቦች ያለው መሆኑ በጥናቱ ተመላክቷል፡፡ አሁን ያለው ትውልድ ባህልን እንደባህልነቱ፣ እሳቤን እንደ እሳቤነቱ ከማስቀጠል ይልቅ ‹‹በግራ አይበላም፣ በግራ በር አይከፈትም፣ በግራ ገንዘብ አይሰጥም›› የሚሉ እሳቤዎችን ብቻ ያውቃቸዋል፡፡ ነገር ግን ‹‹ለምን?›› ሲባል ‹‹ ባህል ስለሆነ›› ወይም ‹‹ነውር ነው›› የሚል ድፍን ያለ የግራ ትዕምርት ትርጓሜን በተሟላ መልክ የማይገልፅ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ እንዲህ አይነት ሂደት

የብሔረሰቡን ዕሳቤ፣ አመለካከትና ፍልስፍናና ለመረዳት አያስችልም፡፡ በመሆኑም ትውልዱ የብሔረሰቡን የግራኝነት ትጓሜን በተሟላ መልኩ እንዲረዳ ከአውድ ጋር የሚሄድ የተሟላ መረጃ ቢሰበሰብና ቢቀረስ መልካም ይሆናል፡፡

# ዋቢዎች


ሰሎሞን ተሾመ፡፡(2007)፡፡ ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ፡፡

ሰለሞን ወንድሙ፡፡(2013)፡፡ የቆሌ ዴጆ ማህበራዊ ፋይዳ ትንተና በካፋ ማህበረሰብ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒተስ ኮሌጅ አማርኛ ት/ት ክፍል፣ ጅማ (ያልታተመ)

በቀለ ወ/ማሪያም፡፡(1996)፡፡ የካፋ ሕዝቦችና መንግስታት አጭር ታሪክ፡፡ ሜጋ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ

ከሳቴ ብርሃን ተሰማ ፡፡(1951)፡፡ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡ አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር(1992)፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 6ኛ ዕትም፣፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡(1962)፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ፡፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት አዲስ አበባ፡፡

ያዴሳ ቶሎሳ ፡፡ (2008)፡፡ አጠቃላይ የትምህርት እና የስራ ላይ ምርምር ዘዴዎችና አተገባበር፡፡ አዲስ አበባ፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ አሳታሚ ድርጅት

ጣሂር አሊ ፡፡(2011)፡፡ በባህላዊ የጋብቻ ሥነሥርዓት ላይ የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶች ትዕምርታዊ ጉዳዮች ትንተና በዲዋ ጨፌ ወረዳ ማሳያነት፤ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

ዘሪሁን አስፋው፡፡(2015)፡፡ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር፡፡ አዲስ አበባ ጃጃው አሳታሚዎች

ፈቃደ አዘዘ።(1991)፡፡ የስነቃል መምሪያ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጻሕፍት ማዕከል፡፡

Alhassan AB, Department of Education,( 2017). Left Handedness, the Bible and the Qur'an: Implications for Parents and Teachers. Journal of Educational Studies. Sule Lamido University, Jigawa Sate, Nigeria

Ben- Amos, Dan (1982). Toward A Defenition of folklore in context. The journal of American folklore.

Dorson, Richard M ed. 1972. Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press.

Goldstein, Kenneth. 1964. Guide for Field Workers in Folklore. Folklore Associates, INC. Hatboro, Pennsylvania, USA.

Gellila H/mariyam.(2021). The Role of traditional Belifs in the conservation of forest; the case of kaffa, southwest Ethiopia. Jimma University

https://www.rxlist.com/left-handed/definition.htm

https://www.sciencedirect.com/topics/neuroscience/left-

**http://www.encyclopedia.uia.org/en**

Iris E. C. Sommer and René S. Kahn.(2009). The history and geography of human handedness. Language Lateralization and Psychosis, Ed. Published by Cambridge University Press.

Jennifer R. States Fisher. (2006). Psychosocial differences between left-handed and Right handed children, Wichita State University

Lange W.(1982). History of the southern Gonga, south western Ethiopia. the University of Michigan

Ohnson, Michelle C.( 2013) "Symbolic and Interpretive Anthropology." In Theory in Social and Cultural Anthropology: An Encyclopedia, Vol. 2, edited by R. Jon McGee and Richard L. Warms, 841-846. Thousand Oaks, CA: SAGE Reference,

Ostrom, E. (1990). *Governing the commons: The evolution of institutions for collective action.* Cambridge: Cambridge University Press.

Sigmund Freud. (1916) A generala introduction to psychoanalysis. By PDF books world.

Stephens. M.(2011). Living Folklore. Utah State University press. Logan Utah. (2nd Edetion)

Toelken, Barre (1996). Dynamics of folklore. Logan; Utah university press.

Zakaria Shanunu, Mohammed Gadafi Ibrahim & Eliasu Alhassan (2022)Cultural Underpinnings on the Use of Left-Hand in Gbanjong Community of the Tolon District of Ghana. Journal of Education and Learning Technology (JELT).

# አባሪ

## ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

| ተ/ቁ | ስም | ዕድሜ | የስራድርሻ | አካበቢ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ወርቁ ወ/ማሪያም | 62 | የባህል አዋቂና የካፊኖኖ መምህር | ቦንጋ |
| 2 | አቶ አባተ አቤቶ | 62 | የባህል ሙዚቃ ተጫዋች | ቦንጋ |
| 3 | አቶ አሰፋ አለማየሁ | 58 | ጉጅራሻና ዳኛ | ቦንጋ |
| 4 | አቶ አጦ ገብሬ | 36 | ባህል አዋቂ | ቦንጋ |
| 5 | አቶ ቦጋለ ኃይለ | 67 | ባህል አዋቂና ፀሐፊ | ቦንጋ |
| 6 | አቶ ፀጋዬ ገ/ማሪያም | 54 | ባህልና ታሪክ አዋቂ | ቦንጋ |
| 7 | አቶ በየነ በቀለ | 60 | ባህልና ታሪክ አዋቂ | ቦንጋ |
| 8 | አቶ ክፍሌ አንጋሞ | 54 | ባህልና ታሪክ አዋቂ | ቦንጋ |
| 9 | አቶ አሰፋ ገ/ማሪያም | 74 | ታሪክ አዋቂ | ቦንጋ |
| 10 | አቶ ተረፈ ወ/ፃዲቅ | 63 | ባህልና ታሪክ አዋቂ | ቦንጋ |
| 11 | አቶ አባተ አንጋሞ | 65 | ባህልና ታሪክ አዋቂ | ቦንጋ |
| 12 | ወ/ሮ ተዋበች ተክሌ | 63 | ባህልናታሪክ አዋቂ እንዲሁም ፀሐፊ | ቦንጋ |
| 13 | አቶ እንዳለ ካሳ | 75 | የሀገር ሽማግሌ | ዴቻ ወረዳ |
| 14 | አቶ ኢሚቶ ገብሬ | 68 | የሀገር ሽማግሌ | ዴቻ ወረዳ |
| 15 | አቶ በላይ ኃይሌ | 67 | የሀገር ሽማግሌ | ዴቻ ወረዳ |
| 16 | መ/ር ታምሩ ወልዴ | 59 | መምህር | ዴቻ ወረዳ |
| 17 | አቶ አጦ ወዶ | 50 | ቃልቻ | ጠሎ ወረዳ |
| 18 | አቶ አለማየሁ አቱሞ | 52 | ባህልና ታሪክ አዋቂ | ጠሎ ወረዳ |
| 19 | አቶ ወንድሙ ገብሬ | 68 | የ‹‹ዮንገቦች›› መንፈስ መሪ ቃልቻ | ጠሎ ወረዳ |
| 20 | አቶ አበበ አዋነ | 65 | ባህልና ታሪክ አዋቂ | ጠሎ ወረዳ |